# አዲስ ዘመን

እንድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 299 ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከጄኔራል አብዱልፈታ አልቡርሃን ጋር ተወያዩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በኬንያ ከሚካሄደው የኢጋድ ስብሰባ ጎን ለጎን ከሱዳኑ ሪፐብሊክ የሽግግር ሉአላዊነት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ጄኔራል አብዱልፈታ አልቡርሃን ጋር ተገናኝተው በወቅታዊ ቀጣናዊ ጉዳይ ላይ የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸውን በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ባሰፈሩት መልዕክት እንደገለጹት፤ ከጄኔራል አልቡርሃን ጋር በነበራቸው የሁለትዮሽ ውይይት ሁለቱ አገራት በሰላማዊ መንገድ ሊሠሩባቸው የሚችሉ በርካታ የትብብር መሠረቶች እንዳሏቸው አረጋግጠናል ብለዋል።

ያለን ትሥሥር ከየትኛውም መከፋፈል የሚበልጥ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ሁለታችንም ያልተፈቱ ቀዳሚ ጉዳዮችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት ቁርጠኝነታችንን ገልጸናል ብለዋል።

የሁለቱ አገራት ጥብቅ ቁርኝት ከልዩነቶቻቸው በላይ እንደሆኑ መነጋገራቸውን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በጋራ ጉዳዮቻችን ላይ በሰላማዊ መንገድ በመወያየት ሰላማዊ መፍትሄ ለመስጠት ቁርጠኛ መሆናችንን ከስምምነት ላይ ደርሰናል ሲሉም አረጋግጠዋል፡፡









## የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መድረኮች ለማድረግ እየተሠራ ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከተሰጣቸው ብቁና ክህሎት ያለው የሰው ሀብት ማፍራት ተልዕኮ ባለፈ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መድረኮች ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለጹ፡፡

ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ትልልቅ ወርክሾፕና ሰፋፊ ቦታ አላቸው፡፡ እነዚህ ቦታዎች ስልጠና ከሚሰጥበት ሰዓት ውጪ ያለ ሥራ ቆመው ይውላሉ፡፡

ይህን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቋማቱ ሥራዎችን ለማከናወን ፋይናንስ የሚጠብቁ ሳይሆን የሥራ ዕድልና ሀብት መፍጠሪያ መድረኮች ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የግሉን ዘርፍ ከተቋማቱ ጋር በማስተሳሰር

የቴክኒክና ሙያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ከፋይል

ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል






## «ተጨማሪ ጥቃትና ጭፍጨፋ እንዳይከሰት ተጋላጭ መንደሮችን በመለየት አስፈላጊው ጥበቃ ይደረጋል»

- አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በወገኖቻችን ላይ ተጨማሪ ጥቃትና ጭፍጨፋ እንዳይከሰት በሁሉም አካባቢዎች ተጋላጭ ቀበሌዎችና መንደሮችን በመለየት አስፈላጊው ጥበቃ ይደረጋል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ።

አቶ ደመቀ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን የተፈጸመውን የንጹሃን ግድያ አስመልክተው የኀዘን መግለጫ አስተላልፈዋል።

በመግለጫቸው በወገኖቻችን ላይ ተጨማሪ ጥቃትና ጭፍጨፋ እንዳይከሰት በሁሉም አካባቢዎች ተጋላጭ ቀበሌዎችና መንደሮችን በመለየት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዲሁም ነዋሪው ራሱን በተደራጀ መልኩ እንዲከላከል የሚሊሻና የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል ብለዋል።

በወለጋ አካባቢ አሁንም አሸባሪው የሸኔ ቡድን በንፁሃን ወገኖቻችን ላይ አሳዛኝ ጭፍጨፋ አካሂዷል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ጥቃቱ የአማራ ብሔር ተወላጆችን ዒላማ ያደረገና ተጠቂዎችን ለመከላከል ሙከራ ባደረጉ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ጭምር ያነጣጠረ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ቡድኑ ሕፃናትን፣ እናቶችን እና ደካማ አረጋውያንን



ለይቶ ተደጋጋሚ ጥፋት በመፈፀም አገር የማፍረስ ግልፅ ተልዕኮ ያነገበ የተስፋ ቢሶች ጥርቅም መሆኑን በተግባር ማረጋገጡን ገልጸዋል።

መንግሥት በመላው አገሪቱ በተለይም ተደጋጋሚ

«ተጨማሪ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኅብረተሰቡ ከጎርፍና መሬት መንሸራተት አደጋ ራሱን እንዲጠብቅ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ አሥር ቀናት የሚኖረው የዝናብ መጠን ጎርፍና መሬት መንሸራተት ሊፈጥር ስለሚችል አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ሲል የኢትዮጵያ ሜትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በቀጣዮቹ አሥር ቀናት እና ሐምሌ ወር የሚከሰተውን የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንታኔ እና በውኃና በእርሻ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳመላከተው፤ በመጪዎቹ አሥር ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች በሚጠበቀው ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ አማካኝነት ከፍተኛ የእርጥበት መኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህ ሁኔታ ለጎርፍ መከሰትና ለመሬት መንሸራተት ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

በተጨማሪም የሚፈጠረው ዝናብ ከመጠን በላይ ማሣ ላይ ውኃ እንዲተኛ ስለሚያደርግ በእርሻ እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ እንቅስቃሴ እንዳያስከትል የማጠንፈፊያ ቦዮችና የጎርፍ መከላከያ እርከኖች በመሥራት ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ኢንስቲትዩቱ አሳስቧል።

በአንፃሩም በመደበኛ ሁኔታቸው የእርጥበት እጥረት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ የሚገኘውን እርጥበት በሰብል ማሣዎች ላይ እንዲቆይ ማድረግ እና ከማሳ ውጪም የውኃ ማሰባሰቢያ ሥራዎች እንዲሠሩ ጠቁሟል። በተመሳሳይም የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኘውን ውኃ በጥንቃቄ መያዝ ይገባቸዋል ብሏል መግለጫው።



በመግለጫው መሠረት በአብዛኞቹ የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፤ በአማራ፣ ትግራይ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ ሲዳማ እና አፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከምዕራብ ኦሞ በስተቀር፤ አዲስ አበባ፣ ሐረሪና ድሬዳዋ እንዲሁም ከሱማሌ ክልል የሲቲና ፋፈን ዞኖች ባሉ ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል።

መግለጫው በወሩ ስላለው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንተና እና ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄም አክሎ ልኳል። በዚህም መሠረት እ.ኤ.አ በመጪው ሐምሌ ወር የክረምት ዝናብ በሁሉም የአገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማና በረዶ አዘል ዝናብ ይከሰታል።

በመጪው ሐምሌ ወር ከደቡብ ንፍቀ ክበብ ወደ አገራችን እየገባ ያለው እርጥበት አዘል ዓየር እየተጠናከረ ሊሄድ እንደሚችል እና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ እና የመካከለኛው የአገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎችን የሸፈነ ዝናብ ቀጣይነት እንደሚኖረው ይጠበቃል ሲል ኢንስቲትዩቱ ገልጿል።

በመሆኑም በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ለተከታታይ ሰዓታት ያለማቋረጥ ዝናብ ሊዘንብ እንደሚችል እንዲሁም በውስን ሰዓት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር ይችላል ያለው የኢንስቲትዩቱ መግለጫ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ተዳፋትና ወንዞች አካባቢ ለጎርፍ መከሰት መንስዔ ሊሆን ስለሚችል ማኅበረሰቡ ተገቢውን ጥቃቄ ሊያደርግ ይገባል ብሏል።

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ላይ ከኦሮሚያ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች እንዲሁም በአዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ መካከለኛውና ምዕራብ ጎንደር እና የክልሉ አብዛኞቹ አካባቢዎች፤ በትግራይ፣ በአፋር፣ በጋምቤላና ቤኒሻንጉል፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም ደቡብ ክልል መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ።

በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ የአርሲ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምሥራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ሁሉም ዞኖች እና ከሱማሌ ክልል ደግሞ የሲቲና ፋፈን ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል ቀሪዎቹ የአገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ የደመና ሽፋንና ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

የጁላይ ወር የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚከናወኑበት መሆኑን የጠቆመው መግለጫው ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅም ጊዜ ሰብሎች የሚያስፈልጋቸውን በቂ ውኃ በበቂ መጠን ያገኛሉ። በተጨማሪም እርጥበት አጠር አካባቢዎች ውኃን ለማከማቸት እና ለግጦሽ ሳርና መጠጥ ውኃ አቅርቦት መልካም አጋጣሚዎችን የሚያገኙበት ወቅት ነው።

## የዓባይ ሲሚንቶ ፋብሪካ ፕሮጀክት ግንባታ በውጭ ምንዛሪ እጥረት መጓተቱ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሁለት አመት እንደሚጠናቀቅ እቅድ ተይዞለት ግንባታው የተጀመረው የዓባይ ሲሚንቶ ፋብሪካ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ሳቢያ ቅድመ ሥራውን ከመጨረስ ፈቀቅ አለማለቱ ተገለጸ፡፡

የዓባይ ኢንዱስትሪያል አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደምስ ተሻገር ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ጥር 16 ቀን 2011 ዓ.ም በተካሄደው የውል ስምምነት መሠረት ወደግንባታ የገባው ይህ ፋብሪካ በሚጠበቀው ፍጥነት ተገንብቶ ወደሥራ እንዳይገባ የግንባታ ግብአት እጥረት ማነቆ ሆኖበታል፡፡

አቶ ደምስ እንዳሉት፤ ፕሮጀክቱ በመቶኛ ይሄን ያህል ደረጃ ደርሷል ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ፕሮጀክቱን ለመጀመር የሚያስፈልጉ የመንገድ፣ የውኃና ኃይል አቅርቦትን የመሳሰሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር የኮንትራትና የዲዛይን ሥራው አልቋል ያሉት አቶ ደምስ፤ የግንባታው ሥራ ባይቆምም ፋብሪካውን ሳይት ላይ ለመትከል የሚያስችለውን ምንዛሬ ማግኘት ባለመቻሉ ግንባታው ተጓቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በግንባታው ሂደት ያለውን ችግር አምኖ መቀበል እንደሚያስፈልግ የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ የዓባይ ሲሚንቶ ፋብሪካ ግንባታው በጊዜው እንዳይጠናቀቅ ያደረገው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ግንባታው በጊዜው ቢያልቅ ክብርና ኩራቱ የባለ አክሲዮኖች፣ የኢንቨስተሮች፣ የመንግሥትና የሕዝቡ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ትልቅ ነው፤ ለአገርም ጠቃሚ ነው፡፡ አብዛኛው የግንባታ ዕቃ በባህሪው ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ይጠይቃል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አልተቻለም ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ያሉት የጸጥታ ችግሮች ለአገራችን የልማት ሥራዎች ከፍተኛ ተግዳሮት መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ደምስ፤ ከድህነት ለመውጣት አገራችን ሰላም ሆና ወደ ልማቱ መዞር መቻል አለበት ብለዋል፡፡

የዓባይ ሲሚንቶ ፋብሪካ ግንባታ ተጠናቆ ወደማረት ከተሸጋገረ በአመት 2 ነጥብ 25 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ማምረት ይችላል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ትልቅ ፕሮጀክት በመሆኑ አሁን ያለውን የሲሚንቶ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያቃልለውም ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካው በቀጥታ ከሚሰጠው ጠቀሜታ ባሻገር በሥራ ዕድል ፈጠራና በልማቱ መስክ በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚሰጥም ጠቁመዋል፡፡

በዓባይ ኢንዱስትሪያል ልማት አክሲዮን ማኅበር ባለቤትነት የሚገነባው ፋብሪካው ጥር 16 ቀን 2011 ዓ.ም የውል ስምምነት ሲያዝ ለግንባታው 24 ወራትን እንደሚወስድና በ28 ወራት ውስጥ የሙከራ ምርት እንደሚጀምር ዕቅድ ተይዞ በ8 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ጠቅላላ ካፒታል የተጀመረ ነበር፡፡

## በክልሉ የወባ ወረርሽኝ እየተስፋፋ መሆኑ ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሳምንት ከዘጠኝ ሺህ እስከ 10ሺህ ሰዎች በወባ ወረርሽኝ እየተጠቁ መሆኑን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ። ወረርሽኙ የክረምቱን መግባት ተከትሎ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቷል።



የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ጤና ቢሮ የበሽታዎች መከላከልና ጤና ማጎልበት ዳይሬክቶሬት የወባ ማስወገድ አማካሪ አቶ ሄኖክ በቀለ እንደተናገሩት፣ ወረርሽኙ የክረምቱን መግባት ተከትሎ በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋና ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ መጥቷል።

እንደ አቶ ሄኖክ ገለጻ፣ በክልሉ ስር ቀድሞም ወረርሽኙ የነበረባቸው ወረዳዎች ነበሩ። የክረምቱ መግባት ተከትሎ ችግሩ እየሰፋ መጥቷል። የወረዳዎቹ ቁጥርና ስፋቱ ይለያይ እንጂ በሁሉም ዞኖች የወባ ወረርሽኝ በስፋት እየታየና ማኅበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ነው።

ክልሉ ከ80 በመቶ በላይ ለወባ አምጪ ትንኝ መራባት ምቹ ነው ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በመሆኑም ወረርሽኙ ከክረምቱ ጋር ተያይዞ በሁሉም ዞኖች በስፋት እየታየና ማኅበረሰቡ ላይ ጫና እያስከተለ መሆኑን ጠቁመዋል።

ወረርሽኙ በጉራጌ ዞን ማረቆ ወረዳ፣ በስልጤ ዞን የሳንኩራ ወረዳ፣ በሀዲያ ምዕራብ ዋዳ ዋቾ፣ ምሥራቅ ቃዋ ዋቾ፣ በኮንታ ጠምባሮ ወረዳና በአጊሎ በከፍተኛ ደረጃ እየተስተዋለ ይገኛል ብለዋል።

በአላባ አካባቢ በጌራ ወረዳ፣ በወላይታ በአራት ወረዳዎች በቦንጊ፣ ዳሞ ሶሬ፣ ሁላታ፣ ቦንጋሌ፣ ወረርሽኙ ልቆ የሚታይባቸው እንደሆኑ የጠቆሙት አቶ ሄኖክ በጋሞ ደግሞ ደረማሎ፣ ከምባታ ዙሪያ፣ አርባ ምንጭ ከተማ ዙሪያ ወረዳ፣ በስፋት እየታየ መሆኑንም አመላክተዋል።

በደቡብ ኦሞ በዳሰነች አካባቢ የተፈናቀሉ ዜጎች ያሉበት ከመሆኑም ባሻገር የስኳር ልማት የሚካሄድበት በመሆኑ ብዙ ሰዎች ያለበት ነው ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በዚህ የተነሳ በዚህ አካባቢ በሽታው በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ከክልሉ በአንደኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ብለዋል።

አቶ ሄኖክ አያይዘውም በባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ሻላና ሌሎችም አካባቢዎች ወረርሽኙ ከፍተኛ ጫና እያደረሰ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም ቤንች ሸኮ ዞን በሚገኙ ደቡብ ቤንች ወረዳ፣ ጉራፈርዳ ወረዳና ሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር፣ በሸካ ዞን የኪ ወረዳና ቴፒ ከተማ አስተዳደር የወባ በሽታ እየተከሰተ ነው ብለዋል።

የወባ በሽታን ለመከላከል አጎበር በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ ይተካ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ባለመተካቱና ነዋሪዎች ያላቸውንም በአግባቡ ባለመጠቀም የመከላከል ሥራ ላይ ክፍተት ፈጥሮ ለበሽታው መስፋፋት መንስኤ ሆኗል።

እንደ አቶ ሄኖክ ገለጻ፤ መደበኛው የኬሚካል ርጭት ሳይካሄድ ሁለት ዓመት አልፎታል፣ የድንገተኛ ርጭት ብቻ ነው እየተካሄደ ያለው። አሁን ደግሞ የድንገተኛውም ጠፍቷል፣ አሁን ላይ አዲስ ኬሚካል ከፌዴራል መንግሥት ተሰጥቷል፣ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ስልጠና እየተሰጠ ነው። ከቀጣይ ሳምንት ጀምሮ ርጭቱ ይካሄዳል።

የፀረ-እጭ ኬሚካል በፌዴራል በኩል የሚቀርብ ነው ያሉት አቶ ሄኖክ፣ ከወቅታዊ የዋጋና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተያይዞ ባለመቅረቡ እንዲቀርብ ጠይቀናል ብለዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ሕክምናው በስፋትና በጥራት እንዲሄድ የሕክምና መድኃኒት በበቂ ሁኔታ እንዲቀርብ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በሰፊው መወያየታቸውን ጠቁመው፤ በክልሉና በፌዴራል በኩልም አቅርቦት ላይ ችግር የለም ብለዋል።

በቅርቡም ለ34 ወረዳዎች የመተኪያ አጎበሮች ተልኮልናል። ከዛሬ ጀምሮ ስርጭት እናደርጋለን ያሉት አቶ ሄኖክ፣ ስምንት ሺህ 100ኪሎ ግራም ኬሚካልም ተሰጥቶናል። 46 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙና ወረርሽኙ ጎልቶ የሚታይባቸውን ቀበሌዎች ርጭት እንዲካሄድ እየተነጋገረን ነው። በቀጣይ ሳምንት ርጭቱን በማካሄድ የማኅበረሰቡን ችግር ለማቃለል እየሠራን ነው ብለዋል።

ወቅቱ የዝናብ በመሆኑ በቀጣይ ሊከሰት የሚችለውን የወባ በሽታ ጫና ለመቀነስ እስከ ቀበሌ ድረስ ንቅናቄ የመፍጠርና የመከላከል ሥራውን አጠናክሮ በማስቀጠል ለበሽታው መስፋፋት መንስኤ የሚሆኑ ውሃ የሚያቁሩ ቦታዎች የማፋሰስና የማዳፈን ሥራ መሥራት፣ አጎበር ማሰራጨት፣ የኬሚካል ርጭትና ሌሎች ለመከላከሉን ሥራ የሚያግዙ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባም አቶ ሄኖክ ተናግረዋል።

# «ንጹሃን ላይ ጭፍጨፋ የፈጸመውን አሸባሪ ቡድን እስከመጨረሻው ተከታትለን እናስወግደዋለን»

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ


ፎቶ - ክፉ ደበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዜጎቻችን ላይ ጥቃት የፈጸመውን አሸባሪ ቡድን ከሕዝባችን ጋር እስከመጨረሻው ተከታትለን እናስወግደዋለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከትናንት በስቲያ በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት፤ በኦሮሚያ ክልል፣ ቄለም ወለጋ ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ጭፍጨፋ እንደተፈጸመባቸው ገልጸዋል።

በዜጎቻችን ላይ በደረሰው መከራ እያዘንን ይሄንን አሸባሪ ቡድን እስከመጨረሻው ተከታትለን ከሕዝባችን ጋር እናስወግደዋለን ሲሉም የመንግሥትን አቋም አሳውቀዋል።

የጸጥታ አካላት ከሚያደርሱበት ዱላ የፈረጠጠው የሸኔ ቡድን በምዕራብ ወለጋ በዜጎች ላይ አደጋ እያደረሰ በመሸሽ ላይ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ቀደም ሲልም፤ በንጹሃን ዜጎች ላይ በሕገወጥ እና በኢ-መደበኛ ኃይሎች የሚደርስ ጥቃት እና መተዳደሪያን ማውደም ተቀባይነት እንደሌለው ማሳሰባቸው ይታወሳል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤኒሻንጉል እና ኦሮሚያ ክልሎች፣ ዋና ዓላማቸው ኅብረተሰቡን ማሸበር በሆነ አካላት የተፈጸመው የሰው ልጆችን ሕይወት የሚቀጥፍ ዘግናኝ ድርጊት የምንታገሰው አይደለም ብለዋል።

ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች ሰላም እና ደህንነትን መመለስ አሁንም ቅድሚያ የምንሰጠው ተግባራችን ነው ሲሉ የመንግሥትን የትኩረት አቅጣጫ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ከነባር ችግሮቿ ተላቅቃ በተስፋዋ ጎዳና እንድትገሠግሥ እየታገልን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ያለፈው ችግሯ ውርስ መከራችንን ሊያረዝመው ይታገለናል። እኛ ደግሞ ተስፋችንን ለማለምለም እንታገላለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰሞኑ በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው ማስፈራቸው የሚታወስ ነው።

በመሆኑም በችግራችን ከተዋጥን ይነግሥብናል። ለተስፋችን ከታገልን እንነግሥበታለን። ስለዚህ ሁላችንም መቻቻልና አብሮነት እንዲያሸንፍ እንጸልይ። ነጋችን ብሩህ እንዲሆን ደግሞ ወጥተን ዛፎችን እንትከል። ተሸናፊው ውርስ ችግር ሊያሳምመን እንጂ ሊያሸንፈን አይችልም ሲሉም መልዕክት አስተላልፈው ነበር።

በቅርቡ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች በተለይ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ክልሎች ዜጎች ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ሕይወታቸውን ማጣታቸውን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መረጃ ያመለክታል።

መንግሥት ሰሞኑን በምዕራብ ወለጋ እና በሌሎች አካባቢዎችም በአሸባሪው ሸኔ እና ሌሎች መሰል ተላላኪ ጽንፈኛ ኃይሎች አማካኝነት፣ በንጹሐን ዜጐች ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ በጽኑ አውግዞ፤ ከጸጥታ ኃይሉና ከኅብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት ጥፋተኞች ላይ ርምጃ እየወሰደ መሆኑን ገልጿል።

# ክልሎች በቄለም ወለጋ የተፈጸመውን የንጹሃን ግድያ አወገዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአማራና የኦሮሚያ ክልል መንግሥታት በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ውስጥ በሚኖሩ ንጹሃን ዜጎች ላይ የደረሰውን ግድያ በማውገዝ የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን ገልጸዋል።

የአማራ ክልል የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ በሰጡት መግለጫ፤ አሸባሪው የሸኔ ቡድን ዛሬም ሰላምን በሚሻው ንጹሃን ሕዝባችን ላይ የሞት ጽዋን የሚያዘንብ የጥፋት መልአክ ሆኗል ብለዋል።

ከማንኛውም የሰው ዘር ጋር በሰላም መኖርን፣ ሠርቶ መበልጸግንና አግኝቶ መደሰትን ብቻ የሚሻው የአማራ ሕዝብም ሆነ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ወገኖች ሰላምን በማይሹ የአገርና የሕዝብ ጠላቶች እንዲህ የመጠቃታቸው ብቸኛው ግብ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማንበርከክ አልመው መሆኑን ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ውስጥ በሚኖሩ ንጹሃን ዜጎች ላይ በደረሰው ጭፍጨፋ ለመላው ሕዝብ መጽናናትን ተመኝተዋል።

እንደ አቶ ግዛቸው መግለጫ ከሆነ፤ ዛሬም ሆነ ነገ የዚህ ችግር ብቸኛው መፍትሔ የሕዝባዊ አንድነት ጠላት እና በጋራ ሠርቶ የማደግ ደመኛ የሆኑ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ኢትዮጵያዊነት የሆኑ ሁሉንም ኃይላት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደ ሕዝብ በአንድነት ታግሎ ማሸነፍ ሲቻል ብቻ ነው።

ይህን መሰል ጥቃቶችን በመፈጸም መሪር ኀዘን ላይ የሚጥሉንን ጠላቶቻችንን ታግሎ ለማሸነፍና ለዚህ ጉዳይ ከሥሩ መፍትሔ ለመፈለግ ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ድምጽ ይህን ድርጊት በመቃወም የመፍትሔው አካል ሊሆን ይገባል ሲሉ አቶ ግዛቸው መናገራቸውን የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ መረጃ ያመላክታል።

ጨፌ ኦሮሚያ በበኩሉ ባወጣው መግለጫ፤ በኦሮሚያ ቄለም ወለጋ ዞን ሐዋ ገላን ወረዳ አሸባሪው ሸኔ በንጹሃን ዜጎች ላይ በፈፀመው ጥቃት የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ገልጿል።

ጨፌው በመግለጫው ሕዝብን ከዚህ አሸባሪ ቡድን ጥቃት፣ እንግልትና ስቃይ ለመታደግ መንግሥት የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላልም ነው ያለው።

ሸኔ በወሰደው ዘግናኝ እርምጃ ንጹሃን ዜጎች መጨፍጨፋቸውን እና በድርጊቱ እጅግ ማዘኑን የገለጸው የጨፌው መግለጫ፤ የአካባቢው ሕዝብ በንቃት ከጸጥታ አካላት ጋር በመሆን አሸባሪው ሸኔን በማያዳግም ጠንካራ ዘመቻ ለማስወገድ እየተወሰደ ያለውን እርምጃ እንዲደግፍ አሳስቧል።

ጨፌው በአሸባሪው ሸኔ ለተቀጠፉት ዜጎች ጥልቅ ኀዘን እንደተሰማውና ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን እንደሚመኝም ገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል መንግሥት አሸባሪው ሸኔን ለመደምሰስ እየወሰደ ያለውን እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጨፌ ኦሮሚያ አስታውቋል።

# «በብዙ ውጣ-ውረድ ታጅበን፤ ትልቅ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል»

## - አፈ-ጉባዔ ታገሰ ጫፎ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- «በብዙ ውጣ-ውረድ ታጅበንም ቢሆን ትልቅ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል» ሲሉ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ ገለጹ፡፡ የምክር ቤቱ አማካሪ እና አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዲሁም የመንግሥት ዋና እና ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዎች በተገኙበት፣ የ11ዱም የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገምግሟል፡፡

የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ ከመንግሥት ምስረታው ጊዜ ጀምሮ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በማሳተፍ፣ ምክር ቤቱ ለአገር ግንባታ ትልቅ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡ እንደ አገር እና እንደ ተቋም የተሠሩ ሥራዎች አበረታች እንደሆኑ እና በቋሚ ኮሚቴዎች የቀረቡት ተጨማሪ ሐሳቦች አስተማሪ ሊሆኑ እንደሚችሉም አመላክተዋል።

ስለሆነም ቆም ብለን በማሰብ፣ አገራችንን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ፣ የሁላችንም ቀና ትብብር ያስፈልጋል ያሉት አቶ ታገሰ፤ የቋሚ ኮሚቴዎች የተቋማት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎቻቸው በውጤት የታጀቡ፣ የሕዝቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ መሆን እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

በጋራ፣ በትብብር እና በቡድን ተቀናጅቶ በመሥራት ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ያስረዱት አፈ-ጉባዔው፤ የውክልና ሥራን በአግባቡ ለመወጣት፣ ከሕዝብ የሚነሱ ቅሬታዎችን መፍታት እና በየደረጃው ካሉ አመራር ጋር ተቀራርቦ መሥራት እንደሚያስፈልግም አመላክተዋል፡፡

አቶ ታገሰ አክለውም፤ የተቋማት ዕቅዶች ከአገሪቷ የ10 ዓመት ፍኖተ-ካርታ ጋር መዛመዱን ማረጋገጥ እንደሚገባ ጠቁመዋል። የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች፤ ከሂደት ይልቅ ውጤትን መሠረት ያደረገ ክትትል እና ግምገማ በማድረግ፣ ተጠያቂነትን እንዴት እናስፍን በሚሉ ጉዳዮች ላይ አጽንዖት ሰጥተው እንዲሠሩም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሏቸው ተቋማት እያንዳንዳቸው ዕቅዶቻቸውን ፈጥነው እንዲልኩላቸው ማድረግ እንዳለባቸውም አያይዘው አሳስበዋል፡፡

ምክትል አፈ-ጉባዔዋ ወይዘሮ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፤ የምክር ቤቱ ግርማ ሞገስ በሥራ የሚገለጽ መሆኑን አስረድተዋል። በመሆኑም፤ ጥሩ የሠሩ ተቋማት የሚበረታቱበት፣ ያልሠሩት ደግሞ የሚጠየቁበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ይገባል ብለዋል፡፡

የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ በበኩላቸው፤ በምክር ቤቱ መሻሻሎች እንዳሉ አንስተው፣ የምክር ቤቱ አባላት ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የክትትል እና ቁጥጥር ሥራቸውን ምክር ቤቱን በሚመጥን ደረጃ ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት፤ እንደ ገቢዎች፣ ንግድ፣ ትራንስፖርት እና ከተማ-ልማት ባሉ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲሁም ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም ትኩረት መስጠት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች በቀጣይ ትኩረት በሚፈልጉ ምጣኔ-ሀብታዊ ዘርፎች ማለትም በአምስቱ የኢኮኖሚ የዕድገት ምንጮች በግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT)፤ ማዕድን እና ቱሪዝም ተመሥርተው የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎቻቸውን ማከናወን እንደሚገባቸውም አሳስበዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎች አመራሮች እና አባላት በሕዝቦች ዘንድ በሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች፣ በሙስና፣ በብልሹ አሠራሮች ላይ ግልጸኝነትን እና ተጠያቂነትን እያረጋገጡ መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም አመልክተዋል፡፡

በፍትሕ ተቋማት፣ በኑሮ ውድነት እና በዋጋ ግሽበት ረገድ ከሕዝቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ መሥራት ካልተቻለ፤ እንደ አገር ትልቅ ውድቀትን ሊያስከትል እንደሚችልም አስገንዝበዋል፡፡

ከግብርና አንጻርም መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በግብርና ሜካናይዜሽን የኩታ-ገጠም እርሻዎችን በማስፋት፤ የበጋ ስንዴን ምርታማነት በመስኖ በማሳደግ፣ ዜጎች ራሳቸውን ከምግብ ጥገኝነት እንዲያወጡ ለማድረግ እና አገራችን ስንዴን ወደ ውጭ እንድትልክ ጭምር በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ለአገራችን ውድቀት ዋናው መንስዔ የትምህርት ሥርዓት ውድቀት በመሆኑ፤ የምክር ቤቱ አባላት የትውልድ ግንባታን አልመው የተቋማትን የትምህርት ጥራት ማሻሻያ መርኃ-ግብሮችን ዓቅም ማጎልበት እንዳለባቸው፣ ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡



የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ረዳት ፕሮፌሰር ምሕረቱ ሻንቆ በኩላቸው፤ የምክር ቤቱ ዋና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት መወጣት መሆኑን ጠቁመዋል። ሂደትን ሳይሆን ውጤትን መሠረት በማድረግ፤ በክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎች የተገኙትን ውጤቶች አንድ ሁለት ብሎ በሪፖርቱ ማስቀመጥ እንደሚገባም አንስተዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ አክለውም፤ ቋሚ ኮሚቴዎች ግብረ-መልስ ሲሰጡ በአምስት ዓመቱ መሪ ዕቅድ ውስጥ ማሻሻል እና ማረጋገጥ በሚል በተቀመጠው ግብ መሠረት ተሠርቷል፣ አልተሠራም የሚለውን ማረጋገጥ (Check and balance) ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

የ11ዱም የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፤ በክትትል እና ቁጥጥር፣ በሕግ-አወጣጥ፣ በፓርላማ ዲፕሎማሲ እና በሕዝብ ውክልና ሥራዎች ምክር ቤቱ በተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት መሠረት፤ የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን አቅርበዋል፡፡

በመሠረተ-ልማቶች፣ በሕንፃ ግንባታዎች፣ በዜጎች ፍትሐዊ የቤት ተጠቃሚነት፣ በትራንስፖርት፤ በመሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች፤ እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ በሚከታተላቸው ተቋማት በውጤት የተመሠረቱ ሥራዎችን በመሥራት፤ የሕዝብን ጥያቄዎች መመለስ እንዳለበትም የምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ አባላት ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ አመልክቷል፡፡

# በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ነፃ የንግድ ቀጣና ለማስጀመር ያለመ የፓናል ውይይት ተካሄደ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነፃ የንግድ ቀጣና በድሬዳዋ ከተማ ፓይለት ደረጃ በፍጥነት ለማስጀመር ያለመ የፓናል ውይይት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ተካሄደ።

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በተዘጋጀው ፓናል ውይይቱ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።

በመድረኩ የተገኙት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ዳግማዊት ሞገስ፣ በኢትዮጵያ ነፃ የንግድ ቀጣና በማቋቋም የዓለም አቀፍ ንግዳችንን በማሳለጥ እያጣን ያለውን ጥቅም ለማግኘትና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እንዲቻል የሎጂስቲክስ ካውንስላችን በፕሮግራም ደረጃ ጸድቋል ብለዋል።



ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ

ይህን የኢኮኖሚ ሪፎርም በሙከራ ደረጃ ለመተግበር የሚያስችል ፓይለት ፕሮጀክት በድሬዳዋ ያሉትን የሎጂስቲክስና የኢንዱስትሪ ፓርክ ፋሲሊቲዎች በመጠቀም እንዲጀመር ከስምምነት ተደርሷል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ነፃ የንግድ ቀጣና መመስረት በብሔራዊ ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ከተካተተ ጀምሮ፤ በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ሰፊ ጥናት ሲከናወን የቆየ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሯ ጥናቱ አሳማኝ ሆኖ በመገኘቱ በካውንስሉ ልዩ የኢኮኖሚክ ቀጣናዎችን ማቋቋም እንደ አንድ የፖሊሲ ፕሮግራም ተይዟል ብለዋል።

ድሬዳዋ ከአዲስ አበባ ቀጥሎ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ማረፊያ ያላት መሆኑ ነፃ የንግድ ቀጣና ለመፍጠር ማስቻሉን ገልጸዋል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኩ እና በደረቅ ወደቡ ያሉትንና አስፈላጊ ግብአቶችንም በመለየት ነፃ የንግድ ቀጣናውን በአጭር ጊዜ አቋቁሞ ወደሥራ ለማስገባት አስፈላጊ ተግባራት እየተከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ብዙ ነፃ የንግድ ቀጣናዎች የሚያስፈልጉ መሆኑንና አገሪቱ እስካሁን የንግድ ቀጣና ስላልነበራት ኅብረተሰቡ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ማስተናገዱን ገልፀዋል።

የፓይለት ነፃ ንግድ ቀጣናውን በአፋጣኝ መመስረት እና በጎረቤት አገራት ነፃ የንግድ ቀጣናዎች ያሉትን የአገራችንን ነጋዴዎች እና ሌሎችን ወደ ነፃ ንግድ ቀጣናው በማስገባት ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የፕሮጀክቱ መሳካት የኢትዮጵያን የሎጂስቲክስ ሥርዓት በማሻሻል በአገራችን ዓለም አቀፍ ንግድ ሥርዓት ላይ ቅልጥፍናን የሚያመጣ መሆኑን ገልፀው፤ ለኢንዱስትሪና ከተሞች ዕድገት፣ ለሥራ ዕድል መስፋፋት፣ ለኑሮ ውድነት መቀነስ፣ በአጠቃላይ ለሁለንተናዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

ነፃ የንግድ ቀጣናውን ወደ ሥራ እንዲገባ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር የኋላእሸት ጀመረ በኩላቸው ነፃ የንግድ ቀጣና ቻይና እና ሌሎች አገራት የተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ አገራችንም ልትጠቀምበት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ነፃ የንግድ ቀጣና ካላቸው ጎረቤት አገራት የተላከው ወደ አገር ውስጥ የሚላከው ገቢ ንግድ ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ «ነፃ የንግድ ቀጣና ሲባል በአንድ አገር ውስጥ ያለ ሌላ አገር እንደ ማለት ነው» ሲሉ ገልጸዋል።

የሎጂስቲክስ ካውንስል በፓይለት ደረጃ አንድ ነፃ የንግድ ቀጣና ለማቋቋም ውሳኔ ላይ መደረሱን አስታውሰው፤ ድሬዳዋ ላይ ቅድሚያ በመጀመር በአገር ደረጃ የማስፋት ሥራ የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ድሬዳዋ ከተማ ለጅቡቲ እና በርበራ ወደቦች ቅርበት ያላት መሆኑ፤ በባቡር፣ በአየር እንዲሁም ከአዋሽ ድሬዳዋ የፍጥነት መንገድ ያለው በመሆኑ ሰፊ የገበያ ዕድል እንዳላት አመላክተዋል።

213 ስኩዌር ኪሎሜትር ልዩ ኢኮኖሚክ ዞን ዝግጁ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አራት ሺህ ሄክታር የያዘ የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲሁም 70 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የወጣበት ደረቅ ወደብ ያለው መሆኑንም ጠቁመዋል።

# የግጭቶች መነሻ የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት ለማደናቀፍ መፈለግ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶች መነሻቸው የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት ለማደናቀፍ የሚያደርጉት ጥረት መሆኑን በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ሰለሞን ተፈራ ገለጹ፡፡ የሱዳን ጠብ አጫሪ ድርጊትም በሌላ ሦስተኛ ወገን የሚነዳ ነው ብለዋል፡፡

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ሰለሞን ተፈራ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የታላቁ ህዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌትና ገበሬው የመኸር እርሻ ልማቱን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚፈጠሩ ግጭቶችና መፈናቀሎች ዋና መነሻው የውሃ ፖለቲካ ነው፡፡ በአገር ውስጥ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን በመጠቀም የውጭ ጠላቶች የልማት ሥራዎች እንዳይከናወኑ እየሠሩ ነው፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ በተለይም ከዓባይ የውሃ ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዓባይ ውሃ ላይ በፍትሐዊ መንገድ የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብትን ለማስተጓጎል የውጭ ኃይሎች እየተስተዋሉ ያሉ አለመግባባቶችን በመጠቀም ልማትን እንዳታከናውን ዘርፈ ብዙ ጫናዎችን እያሳረፉ ነው፡፡

እንደ ፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ ገለጻ፤ በአሁኑ ሰዓት ከህዳሴ ግድቡ ጋር ተያይዞ ግብጽና ተባባሪዎቿ ጫና ለመፍጠር እየሠሩ ነው፡፡ የግብጽ የውሃ ፖለቲካ በብቸኝነት የመጠቀም ፍላጎት ኢትዮጵያ በውሃዋ እንዳትጠቀም ለማድረግ በርካታ እኩይ ሥራዎችን ስታከናውን ቆይታለች፡፡ የህዳሴው ግድብ እንዳይገደብ ከተጀመረም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትና ረጂ ድርጅቶች ድጋፍ እንዳያደርጉና ኢትዮጵያ በውስጧ ሰላም እንዳታገኝ የውስጥና የውጭ ኃይሎችን በመጠቀም የተረጋጋ ኢኮኖሚና ፖለቲካ እንዳታራምድ ለማድረግ እየሠሩ ነው፡፡

ግብጽ በውስጥ ያሉ አለመግባባቶችንና ጎረቤት የሆኑ አገሮችን በመጠቀም አለመረጋጋት እንዲፈጠር ለማድረግ እየሠራች ነው ያሉት መምህሩ፤ ለምሳሌ ሱዳን የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የተዳፈረችው የግብጽን አጀንዳ ለማስፈጸም ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያን ውስጣዊ አመግባባት በማየት ፊቷን ወደ ልማት እንዳታዞር የሚያደርጉበት ሂደት ነው፡፡



**አቶ ሰለሞን ተፈራ**

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የተደቀነው ጉዳይ አገራዊ ነው፤ አገራዊ ጉዳይ ደግሞ በመንግሥት ብቻ የሚፈታ ሳይሆን የሁሉንም ዜጎች የጋራ ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አገሬ ነች ብሎ የሚያስብ ማንኛውም ዜጋ ለሰላምና ለተረጋጋ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የራሱን አሻራ ማሳረፍ ይገባዋል፡፡ የፖለቲካ ኃይሎች በአገራዊ ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም በመያዝ ከውጭ ጣልቃ ገብነትና ሴረኝነት አገርን መታደግ አለባቸው ብለዋል፡፡

ሱዳን ጠብ አጫሪ ድርጊት እየፈጸመች ያለችው የውስጥ ችግሯን ለማርገብና የሕዝቡን ትኩረት ወደ ውጭ ለማምጣትና የግብጽን ፍላጎቶች ለማሟላት እንደፈረስ ሆና እያገለገለች መሆኗን መምህሩ ገልጸዋል፡፡ በውሃ ፖለቲካው ኢትዮጵያ የምታራምደውን የጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ አቋም በበቂ መንገድ ዲፕሎማሲያዊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ከተቃዋሚ ኃይሎችም ከሌሎችም ኃይሎች ጋር መግባባት ለመፍጠር ትልቁ ድርሻ የመንግሥት ነው፡፡ ከጎረቤት አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት የኢትዮጵያን አቋም ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በሚገባ ማስገንዘብ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ከጎረቤት አገራት ጋር ጉርብትናን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ እንደ አገር አካታች የሆነ ብሔራዊ ምክክር ለማድረግ ሁሉም አካላት እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ለዚህም የተቃዋሚ ኃይሎች ለሚደረገው አካታች ብሔራዊ ምክክር ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# «ተጨማሪ ጥቃትና ጭፍጨፋ እንዳይከሰት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጥቃት በሚፈፀምባቸው አካባቢዎች ሕግ ለማስከበር፣ ሰላም እና ፀጥታ ለማስፈን እንዲሁም ዜጎች የተረጋጋ ሕይወት እንዲመሩ ለማስቻል ጠንካራ ርብርብ እያደረገ ቢሆንም፤ አሁንም በተለያዩ አካባቢዎች አሸባሪ ቡድኑ በንፁሃን ዜጎች ላይ ያነጣጠረ ጥፋት መፈፀሙን እንደቀጠለ አቶ ደመቀ ጠቁመዋል።

በማንኛውም መመዘኛ ድርጊቱ በፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ቅንብር እየተፈፀመ ያለ ኢ-ሰብዓዊ እና ዘግናኝ ድርጊት በመሆኑ፤ መንግሥት ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በመተባበር የጀመረውን ሕግ የማስከበር እንቅስቃሴ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፤ በንጹሃን ላይ ተጨማሪ ጥቃትና ጭፍጨፋ እንዳይከሰትም ተጋላጭ ቀበሌዎችና መንደሮችን በመለየት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዲሁም ነዋሪው ራሱን በተደራጀ መልኩ እንዲከላከል የሚሊሻና የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

በመጨረሻም ሕብረታዊ የትግል እንቅስቃሴያችን እንዲከሽፍ ጠላት አስልቶ በርቀት የሚጠባበቀው የሴራ ውጤት በመሆኑ፤ በተደጋጋሚ በደረሰብን ጥፋት ሳንበረከክ አንድነታችንን አጥብቀን በፅናት እንድንጓዝ አደራ እያልኩ በተጎጂ ወገኖች የተሰማኝን ልባዊ ኀዘን እገልፃለሁ ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው በጥቃቱ ማዘናቸውን ገልጸው፤ የሞቱትን ፈጣሪ ነብሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑረው ሲሉ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

በንፁሃን ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ሞት እና መከራ በጣም አሳዛኝ ነው፤ ይህንን አሸባሪ የኦነግ ሸኔ ቡድን በተባበረ ክንዳችን እስከመጨረሻው ማስወገድ ግድ ይለናል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የጥፋት ቡድኑ በእርግጥም በደረሰበት ሽንፈትና ተስፋ በመቁረጡ ያደረሰው ጥቃት ነው። ፈጽሞ መወገጃው መድረሱ ይህ ድርጊቱ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

# የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን የሥራ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማዕከላቱ ለተቋማቱ የሀብት ምንጭ እንዲሆናቸው ማድረግ ያስችላል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ያላቸውን እምቅ እውቀት ተጠቅመው በሚያመርቱት ምርትም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ከፍ ያለ አገራዊ አበርክቶ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚቻልበት ዕድል መኖሩንም ገልጸዋል፡፡

የገበያው የሰው ኃይል ፍላጐትና የክህሎት አለመጣጣም በብዛት እንደ ችግር የሚነሳ ጉዳይ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህም ያለንን አገራዊ አቅም አሟጠን እንዳንጠቀም አድርጎናል ብለዋል፡፡ ችግሩን ከመሠረቱ ለመቅረፍም ሥርዓተ ስልጠናውን ለማሻሻል የሚያስችሉ የመነሻ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የኢኮኖሚ ሽግግሩን እውን በማድረግ ሂደት ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ተብሎ ከተለዩ ዘርፎች መካከል መሆናቸውን ያመለከቱት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ የሙያ ክህሎት ማግኘት እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ባህልና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ላይም በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን ወጣቶች የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ይቀላቀላሉ፡፡ ሆኖም ግን ማኅበረሰቡ ቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ዝቅ ያለ ቦታ የመስጠት የተሳሳተ አመለካከት አለ፡፡

ይህን አስተሳሰብ መቀየር የሚቻለው በግንዛቤ ፈጠራ ብቻ ሳይሆን ተቋማቱን ደረጃ በማሳደግና ከፍ ያለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ በማድረግ ስለሆነ የተቋማቱን ደረጃ ለማሻሻል ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ሚኒስትሯ ጠቁመዋል፡፡ ተቋማቱን የሚቀላቀሉ ወጣቶችም በሚገኘው ክህሎት ራሴን ለውጬ አገሬን የምለውጥበት ትክክለኛው መድረክ ነው ብለው እንዲመጡ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ስልጠና ደግሞ ማየት፣ አገር በቀል እውቀቶችንና ሙያዎችን ወደ ስልጠና በማካተት እነዚህን ሀብቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ በየአካባቢው ያሉ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶችን የሀብት ምንጮች በማድረግ እሴቶቻችንን በአግባቡ ልንጠቀምና ልንጠብቅ እንደሚገባም አስረድተዋል፡፡

ጊዜው የሚጠይቀው ጀግንነት በአገር ወዳድነት ስሜት ድህነትን ተፋልሞ ማሸነፍ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይህን እውን ለማድረግም በአገር ፍቅር ስሜት በየአካባቢው ያሉ ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጠላቶቻችን በእኛ ላይ እንዳይሰለጥኑ!

መሳሪያ ታጥቆ ተስፋ የቆረጠ ኃይል መቼም ቢሆን ሊሄድባቸው የሚችልባቸው የጥፋት መንገዶች ብዙ ዋጋ የሚያስከፍሉ ናቸው። ሁሌም ቢሆን ከተስፋ መቁረጥ በስተጀርባ አስከፊ አደጋዎች ፤ አስጨናቂ ኢሰብአዊ ድርጊቶች እና ከአእምሮ የሚያልፉ ክፉ ሀሳቦች አሉ።

እነዚህ አስከፊ አደጋዎች ፤ አስጨናቂ ኢሰብአዊ ድርጊቶች እና ከአእምሮ የሚያልፉ ክፉ ሀሳቦችን ያለ ብዙ ዋጋ አሸንፎ ለመሻገር ከሁሉም በላይ የጠላትን ሀሳብ በአግባቡ መረዳት እና በዛው ልክ ነቅቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ከፍ ባለ ጥንቃቄ በቅንጅት ተናቦ መንቀሳቀስን ፤ ጥቃቅን ስህተቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ ትርጉም ሰጥቶ ማስላትን ፤ ይጠይቃል።

መሳሪያ ታትቆ ተስፋ የቆረጠ ኃይል መቼም ቢሆን ያገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ለጥፋት ተልእኮው እንደ መልካም አጋጣሚ ወስዶ መጠቀሙ የማይቀር ነው ፤ ይህንን እድል ማሳጣት መጥፊያውን ማቅረብ ያህል ጭምር ነው። ከዚህ አንጻር የቡድኑን እንቅስቃሴዎች በአግባቡ መከታተልና ፈጣን እርምጃ መውሰድ ተገቢነው ።

ቡድኑን በማስወገድም ሆነ የቡድኑን ጥቃቶች በመመከት ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል/የጸጥታና የአስተዳደር / በእኩል ኃላፊነትና ተጠያቂነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል ። የሚዘረጋውም የተጠያቂነት ስርአትም የችግሩን ደረጃ የሚመጥንና ዳግም እንዳይከሰት ማስተማመኛ ሊሰጥ የሚገባ ሊሆን ይገባል።

አሸባሪው ሸኔ በሀገሪቱ እያካሄደ ያለውን የሽብር ተግባር ለማስቆም ሆነ የቡድኑን ግብአተ መሬት ለማፋጠን የጥቃቱ ሰለባ ሊሆኑ በሚችሉ አካባቢዎች ጠንካራ የፀጥታ ስርአት እና ተጠያቂነት ማስፈን ወሳኝ ነው።ያልታዩ ሌሎች አማራጮችንም መመልከት ተገቢ ነው።

በርግጥ ቡድኑ ከታሪካዊ ጠላቶቻችንና ከአሸባሪው ሕወሓት የሽብር ተልእኮ ተቀብሎ መንቀሳቀስ ከጀመረ ውሎ አድሯል፤ በነዚህ ጊዜያትም የብዙ ንጹሀንን ነፍስ አጥፍቷል ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎችን አፈናቅሏል።የልማት ተቋማትንም አውድሟል። ሀገራዊ መረጋጋት እንዳይፈጠር ባለው አቅም ሁሉ ተንቀሳቅሷል፤ እየተንቀሳቀሰም ነው።

በተለይም የሀገሪቱ ዋነኛ ምሰሶ ተደርገው የሚታዩትን የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች መካከል አለመተማመንና ግጭቶችን በመፍጠር ሀገራዊ አንድነቱን ስጋት ውስጥ ለመክተት ማንነትን መሰረት ያደረጉ አሰቃቂ የጅምላ ግድያዎችን አድርጓል ።

በዚህም ህዝባዊ ቁጣን በመቀሥቀስ ለተላላኪዎቹ የጥፋት ተልእኮ መልካም አጋጣሚ ለመፍጠር ብዙ ሰርቷል፤ዛሬም እየሰራ ነው።

በአደባባይ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ጋብቻ በመፈጸምም ፤የቡድኑ የጥፋት አላማ ተሸካሚ መሆኑን አረጋግጧል ፤ በአሁን ወቅትም መንግስት እየወሰደበት ያለውን ጥቃት መቋቋም ሲያቅተው ፤ምንም የማያውቁ ንጹሀን ዜጎች ላይ ኢሰብአዊ ግድያዎችን በመፈጸም የተስፋ መቁረጡን ጥግ እያሳየ ነው።

ቀድሞውንም የፖለቲካ ዓላማ ከማጣት እና ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ግድያን በራሱ የፖለቲካ ግብ አድርጎ ከጅምሩ ሲንቀሳቀስ የነበረው ይህ አሻባሪ ቡድን ፤ በአሁኑ ሰአት ከፍ ባለ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኖ እያደረሰ ያለው ግድያ መላውን ህዝባችንን ያስቆጣና በቡድኑ ላይ በአንድነት እንዲቆሙ እያስገደደ ነው።

ቡድኑ የሚያገኘውን አጋጣሚ በሙሉ ለመጨረሻ የጥፋት ተልእኮው አቅም አድርጎ ለመጠቀም ካለው ከፍ ያለ ፍላጎት አንጻር ዕድሉን እንዳያገኝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአስተዳደር አከላትን ጨምሮ የተለያዩ የአካባቢ የጸጥታ አካላት እየከፈሉት ያለው መስዋዕትነት ለዚህ ዋነኛ ማሳያ ነው።

የቡድኑን የሽብር ተግባር ፊት ለፊት በመጋፈጥ የህይወት መስዋእትነት በመክፈል ላይ ያሉ የአስተዳደር ሆነ የአካባቢ የጸጥታ አባላት ቁጥርም ቀላል አይደለም። በዚህም ቡድኑ ከፍ ባለ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ የገባ ሲሆን የቀቢጸ ተስፋ የሽብር ተግባሩንም በዚያው ልክ እያሰፋ ይገኛል።

ቡድኑን በመጠቀም በሚፈጠር ሃገራዊ አለመረጋጋት ጠላቶችን ሊያስከፍሉን የሚችሉት ዋጋ ከፍ ያለ በመሆኑ፤ ይህንን የሚመጥን ቁርጠኝነት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ጠላቶቻችን ካደቡበት ማድባት አንጻር በዚህ ወቅት ትንሽ ሊባል የሚችል ስህተት ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ሊሰመርበት ይገባል።

በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ያለውን ይህ ኃይል ለማጥፋትና የጥፋት ተልእኮውም ዕድል እንዳያገኘ ሁላችንም በኃላፊነት መንፈስ ልንቀሳቀስ ይገባል፤ ጉዳዩ የአንድ አሸባሪ ድርጅት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የታሪካዊ ጠላቶቻችንና የኛን በጎ የማይፈልጉ ሀይሎች የጋራ አጀንዳ መሆኑንም ማስተዋል ተገቢ ነው።

ከዚህ የተነሳ እንደ ሕዝብ የጠላቶቻችንን አጀንዳ ተረድተን ከስሜት እና ስሜታዊነት ከሚወልዳቸው ጥፋቶች ወጥተን ለዘለቄታው ችግሩን የምንፈታበትን መንገድ መከተል ይጠበቅብናል!

ከአሉባልታና ከልተጨበጡ ወሬዎች ወጥተን በየአጋጣሚው ከቡድኑ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው የህይወት ዋጋ እየከፈሉ ለሚገኙ የአካባቢ የጸጥታ እና የአስተዳደር አካላትም እውቅና ልንሰጥ ይገባል ።

ይህንን ማድረግ ካልቻልን ቡድኑ በያንድንዷ ግድያ ሊፈጥረው የሚችለው ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና እንደ ሀገር ሊያስከፍለን የሚችለው ዋጋ ጠላቶቻችንን በኛ ላይ ሊያሰለጥን የሚችል ስለመሆኑ መዘንጋት የዋህነት ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# በከተማ ግብርና የዋጋ ንረትን እንዋጋ

ይቤ ከደጃች ውቤ

የከተማ ግብርና በበርካታ ሀገራት የሚተገበር ሲሆን የአደጉ ሀገሮች አብዛኛውን የከተማ የምግብ ፍጆታቸውን የሚሸፈኑት በከተማ ግብርና ነው።በዓለማችን 125 ሚሊዮን የሚጠጉ ነዋሪዎች በከተማ ግብርና ተሳታፊ እንደሆኑ ሰነዶች ያሳያሉ።ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች በዲግሪ እና በሰርተፍኬት መርሃ ግብራቸው የከተማ ግብርናን አካተው ያስተምራሉ። ይህም ዘላቂነት ያለው የከተማ ምግብ ስርዓትን በተሳካ ሁኔታ ቀርጾ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡

በጆርጂያ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ግብርና ፕሮግራም ዳይሬክተር ቦቢ ዊልሰን ‹‹የአትላንታ የከተማ አትክልት እንክብካቤ ፕሮግራም ዘርን ከመትከል እና ሲያድግ ከመመልከት ያለፈ ነው። ማኅበረሰቦችን ስለማሳደግ፣ አዳዲስ አመራሮችን ማሰልጠን፣ የተራቡትንና ቤት የሌላቸውን መመገብ፣ የገበሬዎች ገበያ ስለማቋቋም እና በአትክልት ከወጣቶችና ጎልማሶች ጋር መሥራት ነው።››ይላሉ።የከተማ ግብርና ስንል አዝዕርቶች አትክልቶችና እንስሳት እርባታን የሚያካትት ሲሆን አትክልትና ፍራፍሬዎች ሳይበስብሱ ፣ሳይደርቁ በቅርበት ለነዋሪዎች በቶሎና በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ ያስችላል። ወደ ሀገራችን ስንመጣ ግብርናን ከገጠርና ከሠፊ መሬት ጋር ብቻ የማያያዝ ልምድ በስፋት ይስተዋላል።በበኩሌ የከተማ ግብርና የሚለውን ስም ያወቅኩት በቅርቡ ነው።እንደ አዲስ አበባ በመሳሰሉ ትልልቅ ከተሞች የከተማ ግብርናውን ሥራዬ ብሎ የሚያካሂደው አለ ወይ? የሚለውም ራሱን የቻለ ጥያቄ ነው።ቀደም ሲል (ከሃያ ዓመት በፊት) ለፒያሳ አትክልት ተራ ከመሀል ከተማ አንዳንድ ቦታዎች አትክልት ተመርቶ ለሽያጭ ይቀርብ ነበር።በወቅቱ የእርሻ ትምህርት በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ይሰጥም ነበር ። ነገር ግን ቀስ በቀስ ከከተማዋ መስፋፋትና ከነዋሪዎች ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ ምርቱ ከከተማው ውጪ ካሉ አካባቢዎች ብቻ መምጣት ጀመረ።

በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለከተማ ግብርና ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ እያየን መሆኑ ግን በራሱ አንድ ተስፋ ሰጪ ጅምር ነው። ይህም ሆኖ ወንዛ ወንዙ ሁሉ መጸዳጃ ቤትና ቆሻሻ መጣያ (ማለትም የማይበሰብሱ ላስቲኮች ፌስታልና ሃይላንድ የሚጣልባት) ለሆነባት ሸገር የከተማ ግብርና መጀመሩ የግብርና ባለሙያ ክትትልና ጥንቃቄ የሚያሻው ነው።እስከ ቅርብ ግዜ በአንዳንድ የከተማዋ ቦታዎች አትክልት በሚመረትበት አምራቾቹን የሚደግፍ ባለሙያ አልነበረም ።

ዛሬ ቢያንስ መንግስት ለመደገፍ አለሁ እያለ በመሆኑና ዘርፉ ከተሠራበት ሰዎች ራሳቸውን ከመመገብ አልፈው በመሸጥ ገቢ ሊያገኙበት የሚያስችል በመሆኑ ለከተማ ግብርና የሚሆን ቦታ ያለው ሁሉ በሙሉ በአቅሙ በማምረት የዋጋ ንረትን ሊዋጋ ይገባል። ሰሞኑን በከተማ ግብርና ቲማቲም ፣ጎመን፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ድንች፣ ሀባብና ሸንኩርት ወዘተ በማምረት ከራሳቸው ፍጆታ አልፈው ለሽያጭም እያቀረቡ መሆናቸውን ከኅብረት ሥራ ኮሚሽን የወጣ መረጃ አሰምቶናል።ይህም በትኩረት ከሠራንበት የከተማ ግብርና ለምግብ እህል እጥረትና ለዋጋ ንረት መፍትሔ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ያመላክታል፡፡ በአዲስ አበባ አብዛኛው ነዋሪ የራሱ መኖሪያ ቤትና ግቢ የሌለው ከመሆኑ አኳያ ያለው የመሬት ጥበት ለከተማ ግብርና አዳጋች እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ገን የከተማ ገብርና በመሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በህንፃዎች ጣራ፣ በበረንዳዎችና በጓሮዎች በሠፊው ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

በሌላ በኩል በየሰፈሩ ለከተማ ግብርና ሊውሉ የሚችሉ በግለሰብ ባለቤትነት ያልተያዙ ቦታዎች ቢኖሩም ከቆሻሻ ማጠራቀሚያነት የዘለለ ፋይዳ ሲሰጡ አይታይም። ዛሬ ዛሬ በአንዳንድ አካባቢዎች ክፍት ቦታዎች በአበቦች በዛፎችና በአረንጓዴ ተክሎች ተውበው፤ የሚያረኩና የሚማርኩ ሆነው ማየት እየጀመርን ነው። በተጨማሪ በግብርና ሙያ የሚተዳደሩ በከተማው ዳርቻ ያሉ ነዋሪዎች የጓሮ አትክልት እያለሙ ለከተማው ነዋሪ ቢያቀርቡ ራሳቸውንም ወገናቸውንም መጥቀም የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው።

ሠፊ ግቢ ያላቸው በተለይ በቦሌ፤ ኮተቤና ኮልፌ አካባቢዎች ያሉ ነዋሪዎች ጓሯቸውን ቆፍረው የጓሮ አትክልት ሲያለሙ አይታይም። ምክንያቱን ለእነሱ ብንተወውም ሽምቼ መብላት እየቻልኩ ምን አደከመኝ? ከሚልና ትኩረት ካለመስጠት የሚነሳ ይመስላል። ጥቂቶች ሠፊ ግቢ ቢኖራቸውም መዝናኛ መሥራትን እንጂ የጓሮ አትክልት ማምረትን አያስበውም።

በመዲናዋ በዘንድሮው የመኸር ወቅት እንኳ ከአምስት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደሮችና ከተማ ግብርና ኮሚሽን አስታውቆ ነበር። ይህም ‹‹ምግባችን ከደጃችን›› በሚል መሪ ቃል ክረምት ከመግባቱ በፊት በስድስት ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ አርሶ አደሮች ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የእርሻ ማረሻ ትራክተር ፣ የአፈር ማዳበሪያና ልዩ ልዩ ምርጥ ዘር ድጋፍ ተደርጎ ነው። ያለንበት ወቅት ክረምት መባቻ እንደመሆኑ ትምህርት ቤቶች ይዘጋሉ።

በዚህም ሠፋፊ መሬት ባላቸው የትምህርት ቤት ግቢዎች የጓሮ አትክልት በማምረት የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ እንዲጠቀም ብሎም በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ነዋሪ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ ቢያመቻቹ ፋየዳው ከፍተኛ ነው።ባለፈው ዓመት በአስር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድንች፣ ሽንኩርት እና ቲማቲም በማልማት በትምህርት ቤቶቹ ለሚካሄደው የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በሽያጭ እያቀረቡ ገቢ ማግኘታቸው፤ ዘርፉ በትኩረት ከተሠራበት ለነዋሪው መትረፍ እንደሚችል አንዱ ማሳያ ነው።

በታላቁ ቤተመንግሥት የጓሮ አትክልት በማምረት ለነዋሪዎች ሲታደል ከመገናኛ ብዙሃን ሰምተናል፡ ፡ይህም ሌሎች ሠፋፊ ግቢ ያላቸው መንግሥታዊ ተቋማት ተመሳሳይ ምርቶችን አምርተው ሠራተኞችና የአካባቢው ነዋሪ በርካሽ ዋጋ እንዲጠቀም ቢያመቻቹ የከተማ ግብርናው ከጋዜጣዊ መግለጫ በዘለለ ስኬታማ ይሆናል።ቀደም ብሎም አንዳንድ የመዲናዋ ጤና ጣቢያዎች ባላቸው ቦታ በከተማ ግብርና እያለሙ ሲጠቀሙ አስተውለናል።ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም ባላቸው ቦታ በከተማ ግብርና እየተሳተፉ ግዴታቸውን እየተወጡ ለህዝቡ ምሳሌ ቢሆኑ መልካም ነው።

በተጨማሪ በግብርና ሙያ የሚተዳደሩ በከተማው ዳርቻ ያሉ ነዋሪዎች የጓሮ አትክልት እያለሙ ለከተማው ነዋሪ ቢያቀርቡ ራሳቸውንም ወገናቸውንም መጥቀም የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው። በፊኒፊኔ ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች በከተማ ግብርናው አዝዕርትና አትክልት በማምረት ለሸገር ነዋሪ እየሸጡ ከኑሮ ውድነት ችግር ራሳቸውን ሊያወጡ የሚችሉበት ዕድሉ ሠፊ ነው።

ባጠቃለይ የከተማ ግብርና በአግባቡ መተግበር ከተቻለ ጥቅሙ ድርብ ድርብርብ ነው በአንድ ወገን በከተማ ግብርና አምራቹ ሲጠቀም ሸማቹም በተመጣጣኝ ዋጋ የሚፈልገውን ምርት ያገኛል።እንደ ሀገር ደግሞ የአየር ሁኔታ እንዲስተካከል በማድረግ የህብረተሰቡን ጤና መጠበቅ ይቻላል። በመሆኑም የዋጋ ንረትን ለመቀነስ፤ የአየር ብክለትን ለመከላከል፤ ከተማችንን ጽዳትና ውበት ለማላበስና ጤናችንን ለመጠበቅ በቻልነው ሁሉ በከተማ ግብርና እንሳተፍ መልእክቴ ነው፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# «የኃይል መቆራረጥ አለ፤ ነገር ግን በእኛም በኩል ችግሩን ለማቃለል እየሠራን ነው»

**አቶ በቀለ ክፍሌ**

**የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ**

**ምህረት ሞገስ**

ክረምትን ተከትለው በአዲስ አበባ ከሚከሰቱ ተደጋጋሚ አጋጣሚዎች መካከል የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ዋነኛው ነው። ዝናብ ጠብ ባለ ቁጥር የሚቋረጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሰኔ ግም ማለቱን ተከትሎ በየአካባቢው የነበረ ተለምዶውን እያስቀጠለ ነው። በኤሌክትሪክ መቆራረጥ በተደጋጋሚ አቤቱታዎች ከሚቀርብባቸው መካከል በዋናነት ጀሞ 1 እና ጀሞ 2 የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ አስኮ፣ ብርጭቆ እና አራት መንታ ፣ ሃያት እና ፈረንሳይ ተጠቃሽ ናቸው። እንዲሁም በሌሎች የተለያዩ አካባቢ እና መንደሮች ተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ እያጋጠመ ስለመሆኑ ጥቆማ ሰጪዎቻችን አቤቱታ በማቅረብ ላይ ናቸው። የቀረበውን አቤቱታ ይዘንና የራሳችንንም ትዝብት አክለን ወደ አዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ብቅ ብለናል። የአገልግሎቱ የኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ክፍሌ ጋር ከኤሌክትሪክ መቆራረጥና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ያደረግነውን ቃለመጠይቅ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ላይ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መቆራረጥ የተለመደ ቢሆንም፤ መሻሻል አሳይቶ ነበር። ሆኖም ከአንድ ዓመት ወዲህ እጅግ ተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ እያጋጠመ መሆኑን እና በፍጥነት የኃይል መቆራረጥ ችግርን በመፍታት በኩል ክፍተት እንደሚታይ በመጠቆም ነዋሪው አቤቱታ እያቀረቡ ነው። በእርግጥ ከአንድ ዓመት ወዲህ በተለይ በክረምት ኃይል በስፋት የተቋረጠበት የተለየ ምክንያት ይኖር ይሆን ?**

**አቶ በቀለ፡-** በእኛ በኩል የተለየ መቆራረጥ አለ የሚል እምነት የለንም። ክረምት በመሆኑ የተለመደ መቆራረጥ ያጋጥማል። በጥገና ክፍል ያለው የቴክኒክ ክፍሉ መደበኛ ሥራው ጥገና ነው። የቴክኒክ ክፍሉ ክረምት ላይ የቅድመ መቆራረጥ ሥራን ይሠራል። ስለዚህ ከፕሮጀክት እና ከመልሶ ግንባታ ቀጥሎ ጥገና ላይ በመደበኛነት እየሠራን መሆኑ መታወቅ አለበት። በዋናነት እንዳይቆራረጥ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንገኛለን ስንል በተለይ የፓወር ቻይና ካምፓኒ 600 ኪሎ ሜትሩን ጨርሶ መሥራቱን ማሳወቅ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ግልፅ አይደለም። ካምፓኒው የዘረጋው ነባር መስመሮችን ነው ወይስ አዲስ መስመር ዘረጋ ? በደንብ ያብራሩት።**

**አቶ በቀለ፡-** 600 ኪሎ ሜትሩን ግልፅ ለማድረግ ቅድሚያ መታወቅ ያለበት፤ የኃይል መቆራረጥ ማለት ከኃይል ማከፋፈያ ጣቢያው ወጥቶ ወደየሠፈሩ የሚሔድ ለየትራንስፎርመሩ የሚሰጥ ኃይል እዛ ላይ ተቋረጠ ማለት ነው። መልሶ ግንባታ ያስፈለገበትም ምክንያት አዲስ አበባ የኤሌክትሪክ መስመር ሲዘረጋ በዛ ጊዜ የነበረውን የኤሌክትሪክ ፍላጎት መሠረት አድርጎ ኔትወርክ ተዘርግቷል። ትራንስፎርመር ተቀምጧል። አሁን አርጅቶ የሚታየው እና ለመውደቅ ያዘነበለው ምሰሶ ያኔ ለነበረው ፍላጎት በቂ ቢሆንም አሁን ግን ከምሰሶ ማርጀት በተጨማሪ ኬብሎቹም አሁን ያለውን የኃይል ፍላጎት የመሸከም አቅም የላቸውም።

ነባሩ የመሸከም አቅም እንዲኖረውና የማኅበረሰቡን ፍላጎት ዕድገትን መሠረት በማድረግ ይሠራ ስለተባለ ያንን መሠረት በማድረግ እየተሠራ ነው። ይህ ማለት አዲስ አበባ ላይ ወደ 138 ማከፋፈያ ጣቢያዎች አሉ። እነዚህ ማከፋፈያዎች ለአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ዙሪያ ላሉ ለኦሮሚያ ልዩ ዞኖች ለሰበታ፣ ለሱሉልታ ወይም ሌሎች አቅራቢያዎችንም ያካተተ ነው። እነዚህ ማከፋፈያዎች በተጨማሪነት የመሐል ከተማውንም ይይዛሉ።



600 ኪሎ ሜትር ተሠራ የምንለው እነዚህን መስመሮች በማጠናከር ነው። እነዚህ ላይ የመልሶ ግንባታ ሥራ ተሠራ ማለት እንጨቱን ወደ ኮንክሪት፤ ኬብሉንም በመቀየር አቅሙን የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል ማለት ነው። ይሔ ሲሆን ንፋስም ሆነ የኃይል መጠን መጨመር ችግር አይፈጥርም። ስለዚህ የኃይል መቆራረጥ ይቀንሳል። በሌላ በኩል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መቆራረጥ ሲታይ የነበረው ቀድሞ 600 ኪሎ ሜትር ሲሻሻል ስለነበረ ነው። በመቀጠል በአፍሪካ ልማት ባንክ የሚሠራ ሁለተኛው ምዕራፍ የ400 ኪሎ ሜትር ሥራ ተጀምሯል።

**ከ138 መስመሮች መካከል ትልልቅ ችግር ያለባቸው መስመሮች እየተመረጡ ሥራው ይሠራል፡፡ ካሉን ማከፋፈያዎች ተነስተው ወደየመንደሩ ይሔዳል። ነገር ግን ካለው ፍላጎት አንፃር እየተሠራ ያለው በቂ አይደለም፡፡ በአንድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከተፈለገ ደግሞ ከፍተኛ ገንዘብ ይፈልጋል፡፡ አሁንም የሚሠራው በብድር ነው፡፡ በሀገርም ሆነ በተቋም ደረጃ ያለው አቅም የሚታወቅ ነው፡፡ ስለዚህ የኃይል መቆራረጥ አለ፡፡ ነገር ግን በእኛም በኩል ችግሩን ለማቃለል እየሠራን ነው**

◇◇◇◇◇◇

**አዲስ ዘመን፡- 600 ኪሎ ሜትር ሸፍነናል ሲሉ የአዲስ አበባ አካባቢ መስመር ታድሶስታል የሚባለው የትኛው አካባቢ ነው?**

ከ138 መስመሮች መካከል ትልልቅ ችግር ያለባቸው መስመሮች እየተመረጡ ሥራው ይሠራል። ካሉን ማከፋፈያዎች ተነስተው ወደየመንደሩ ይሔዳል። ነገር ግን ካለው ፍላጎት አንፃር እየተሠራ ያለው በቂ አይደለም። በአንድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከተፈለገ ደግሞ ከፍተኛ ገንዘብ ይፈልጋል። አሁንም የሚሠራው በብድር ነው። በሀገርም ሆነ በተቋም ደረጃ ያለው አቅም የሚታወቅ ነው። ስለዚህ የኃይል መቆራረጥ አለ። ነገር ግን በእኛም በኩል ችግሩን ለማቃለል እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኤሌክትሪክ መቆራረጥ በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍጥነት ያለው ጥገና ለምን አይደረግም?**

**አቶ በቀለ፡-** ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ኤሌክትሪክ የሚቋረጠው እንደሚታወቀው በብልሽት ምክንያት ነው። የብልሽቱ ምክንያት እና የት ቦታ ላይ እንደተቋረጠ ሊታወቅም ላይታወቅም ይችላል። መስመሩ የተቋረጠበትን ምክንያት ለማረጋገጥ እያንዳንዱን መስመር የሲኒ መሰንጠቅ ድረስ ማየት ሊያስፈልግ ይችላል። እስከ 100 ትራንስፎርመር ድረስ የተቋረጠበትን ለማወቅ የሚፈለግበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። የሥራው ሂደት መዘግየትን ሊያስከትል ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኃይል ሲቋረጥ ምክንያቱን ወዲያውኑ የሚያሳውቅ ቴክኖሎጂ የለም እንዴ?**

**አቶ በቀለ፡-** በእርግጥ በአዲስ መልክ የሚሠራው ሥራ የቱ ጋር ችግር እንዳጋጠመ ይጠቁማል። ከዚህ በኋላ በታደሱት መስመሮች ላይ ቢሮ ቁጭ ብሎ ኃይል የቱ ጋር እንደተቋረጠ ይታወቃል። የጥገና ክፍል ቡድኑ ሔዶ ይሠራል። ፕሮጀክቱ ይሔንንም ያካትታል። ማበዳደሪያ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችንም ይዟል። ብልሽት ሲያጋጥም ኃይል ሲቋረጥ መስመሮች ሁሉ አይቋረጡም። ሁሉም መስመሮች የሚቋረጡት በብልሽት ምክንያት ወይም ጥገና ሲካሔድ ለጥንቃቄ ሲባል ብቻ ነው። ይህ ሲባል የፕሮጀክት ሥራውም ሲሠራ ኃይል ይቋረጣል። ያለበለዚያ ሥራውን መሥራት አይቻልም። ለጥንቃቄ ጥገና ስናደርግም እናቋርጣለን።

አዲስ ደንበኞች ሲመጣ እነርሱን ለመቀላቀል ወደ ስምንት መስመሮች በየቀኑ ለ30 ደቂቃ እና ለአንድ ሰዓት እናቋርጣለን። ይሄ ማለት አዳዲስ ደንበኞች ትራንስፎርመር ካልተቋረጠ ማገናኘት አይቻልም። ነገር ግን ከኋላ ቀድሞ ሥራው ከተጨረሰ በኋላ ለማገናኘት ብቻ ኃይል የሚቋረጠው ለ30 ደቂቃ ነው። ይሔ መደበኛ ነው። ሌላው ለጥገና ተብሎም ይቋረጣል። ለምሳሌ ብልሽት ከተገኘ በኋላ ብልሽቱ ረዥም ከሆነ ለማስተካከል እና ለመሥራት ሲባል ይቋረጣል። የመሬት ውስጥ (የአንደር ግራውንድ) መስመር ላይም አንዳንድ ቦታዎች ላይ ለምሳሌ ሃያት አካባቢ ብልሽቱ የቱ አካባቢ እንደተፈጠረ ለማወቅ እና ጠግኖ ወደ አገልግሎት ለማስገባት ጊዜን ይጠይቃል። ስለዚህ በዚህ ጊዜ ኃይል ይቋረጣል።

**አዲስ ዘመን፡- በዋናነት በአዲስ አበባ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መቋረጥ አሰቃይቶናል የሚሉት የጀሞ 1 እና የጀሞ 2 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ናቸው። ሌሎችም የአስኮ እና ብርጭቆ አካባቢ ነዋሪዎችም አራት መንታ አካባቢም በተደጋጋሚ ኃይል ይቋረጣል ይላሉ። በዋናነት በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ኃይል የሚቋረጥበት ምክንያት እና ችግሩ የቀጠለበት ሰበብ ምንድን ነው? በእነዚሁ አካባቢዎች በቅርብ ርቀት አገልግሎት ሳይቋረጥ እነርሱ ጋር ለምን ተደጋጋሚ ኃይል ይቋረጣል?**

**አቶ በቀለ፡-** ይሔ የአገልግሎት አሰጣጡ ባህሪ ነው። ለምሳሌ ሁለት ጎረቤታሞች ቢኖሩ የአንዱ ቤት በርቶ የሌላው ቤት ሊጠፋ ይችላል። ትራንስፎርመር ሲመጣ ሶስት ፌዝ ይይዛል። ጭነት ከበዛ በተደጋጋሚ ፊውዟ ትቃጠላለች። የአንዱ ቤት መስመር ከዛች በተደጋጋሚ ከምትቃጠል ፊውዝ ላይ የተወሰደ ሊሆን ይችላል። ሌላኛው ደግሞ ጭነት ካልበዛበት መስመር የተወሰደ ከሆነ አንዱ ቤት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ኖሮ አንደኛው ቤት ላይኖር ይችላል። ይሔ ትልቅ ቅሬታ ይፈጥራል። ጭነት አንዱ ላይ እንዳይበዛ የማቻቻል ሥራ እየሠራን ነው።

በሌላ በኩል ከ138ቱ መስመሮች መካከል አንዱ ተደጋጋሚ የኔትወርክ ብልሽት ሊያጋጥመው ይችላል። ሌላኛው ደግሞ በመልሶ ግንባታ የተጠገነለት ሊሆን

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

ይችላል። ስለዚህ አንድ ቤት ወይም አንድ አካባቢ የኤሌክትሪክ ኃይል ኖሮ ሌላው ጋር አለመኖር ያጋጥማል። ከዛ ውጪ ሆን ተብሎ ኃይል እንዲቋረጥ አይደረግም። ሥርዓቱ ራሱ ሆን ብሎ ለማቋረጥ የሚስችል አይደለም። በዋናነትም ኃይል የሚቋረጠው ከእኛ አይደለም። ሲቋረጥ የሚቋረጠው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ነው። የእኛ ሥራ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የገዛነውን ማከፋፈል ነው። ሲቋረጥ የሚቋረጠው ከእነርሱ ጋር መሆኑን ሕዝቡ ማወቅ አለበት። የእኛ መስመር ችግር ሲያጋጥመው የእነርሱ ኃይል ይቋረጣል።

**አዲስ ዘመን፡- በኃይል ሻጫቹ ምክንያት ኤሌክትሪክ የሚያቋርጥበት አጋጣሚ የለም?**

**አቶ በቀለ፡-** እነርሱ ከማከፋፈያ ጣቢያ ቀጥሎ ትራንስሚሽን አላቸው። ዋናው ከማከፋፈያ ጣቢያ ከተቋረጠ አበቃ ማለት ነው። ነገር ግን እነርሱ መስመሮችን ያወጡልናል፤ እንደኛ ፍላጎት የማከፋፈያ ጣቢያ ማስፋፊያ ይሠራሉ። እኛም ከእነርሱ ወስደን ለሕዝቡ እናደርሳለን። እነርሱ አካባቢ ምንም ችግር የለም። የኤሌክትሪክ ኃይል አለ። ከሌለ ለሕዝብ የኤሌክትሪክ እጥረት መኖሩ ይነገራል። እጥረት ካለ መኖሩን የሚናገረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ነው። የእኛ ሥራ የገዛነውን ማከፋፈል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሰሜኑ ጦርነት ብዙ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫዎች ወድመዋል። ያንን ለማስተካከል እና ወደ ነበረበት ለመመለስ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ብዙ ሥራዎችን ሠርተዋል። እዚህ ላይ በመጠባበቂያነት ለጥገና በሚል የተያዙ ግብዓቶች በሙሉ ወደ ተጎዳው አካባቢ ሔደዋል ሲባል ነበር። አሁን ተደጋጋሚ የኃይል መቋረጥ ከጦርነቱ ጋር የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል? ምክንያቱም አዲስ አበባ ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እየተቋረጠ ነው የሚባለው ክረምት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ክረምቱ ከመግባቱ በፊትም በስፋት ይቋረጥ ነበር። አሁንም ይኸው ቀጥሏል። የግብዓት እጥረት አለ?**

**አቶ በቀለ፡-** እንደተባለው በአዲስ አበባ ደረጃ ለጥገና የግብዓት እጥረት አላጋጠመም። በእርግጥ በተቋም ደረጃ ግብዓቶች ወደ ወደሙ አካባቢዎች ሔደዋል። ሌላው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ያን ያህል ከባድ ችግር አላጋጠመንም። ነገር ግን ጀሞ አካባቢ አንድ የእነሱ ፓወር ትራንስፎርመር ተቃጥሏል። ለሁለት ወር ብዙ መከራ ሆኖ ነበር። ምክንያቱም ትራንስፎርመሩ ሰባት መስመሮችን የያዘ ነበር። ሰባቱን መስመሮች ከሌላ ቦታ በማበዳደር ሲሰጥ ነበር። በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ሲሰቃይ እንደነበር አይካድም። በማበደርም ኤሌክትሪኩን የምንሰጠው ለአራት ሰዓት ብቻ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ከማበዳደር እና በሰዓት ከመስጠት ይልቅ በአዲስ መተካት አይሻልም ነበር?**

**አቶ በቀለ፡-** መተካት ያለባቸው እነርሱ ናቸው። የተቃጠለባቸው የእነርሱ ሲሆን ተክተው ኃይል መስጠት ያለባቸውም እነርሱ ናቸው። እኛ ግን ደንበኞቻችን ኤሌክትሪክ እንዳያጡ ከሰበታ የሚገኘውን ከአንፎ እና ከሌሎችም ንዑስ ጣቢያዎች ኃይል በማበደር ከፍተኛ ጥረት በማድረግ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ጀሞ ላይ አየር ጤናን ጨምሮ ሰባት መስመር ማለት በጣም ብዙ ነው። ያንን ሁሉ በማበዳደር ተክተናል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን እነርሱ ተክተዋል?**

**አቶ በቀለ፡-** ለጊዜው መረጃ የለኝም። በእኛ በኩል ግን በማበዳደር ችግሩን አቃለነዋል። ከመካኒሳ ከአንፎ እያልን ለማሟት ሞክረናል። አሁን በአጠቃላይ ችግሩ ተቃሏል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ጀሞ ብቻ አይደለም፤ ከላይ እንደገለፅኩት አስኮ እና ሌሎችም አካባቢዎች ላይ ተመሳሳይ ችግር አለ። ሰዎች ደግሞ አሁን ላይ በኤሌክትሪክ በኩል ጥገኞች ናቸው? ሥራቸው ከኤሌክትሪክ ጋር የተቆራኙ ሰዎች ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ በቀለ፡-** አስኮ አካባቢ ብርጭቆ እና አራት መንታ አካባቢ አንደርግራውንድ መስመር ብልሽት አጋጥሞ ነበር። ሃያት ፣ ቃሊቲ ፣ ቡልቡላ እና ሌሎችም አካባቢዎች ላይ ግራውንድ ኬብል ሲበላሽ ኃይል ይቋረጣል። የት አካባቢ እንደተበላሸ አይታወቅም። ያ ግራውንድ ኬብል እስኪገኝ መከራ ነው። ኮልፌ አካባቢም ከፍተኛ ጭነት ያለበት እና በጣም የምንቸገርበት አንድ መስመር አለ። እነዚህ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ላይ ትኩረት ይሰጣል። የተለየች ትንሽ አካባቢ ላይ ከሆነ ቅርብ ላለው ማዕከል ሔዶ መንገር ነው። እንዲህ አይነት ችግር ይኖራል። ትራንስፎርመሩ ጭነት በዝቶበት ፊውዝ ሊቃጠል ይችላል። ይህ በአስቸኳይ ጥገና ይስተካከላል።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ነዋሪ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ነው። የነበረው ሕዝብም ቢሆን ፍላጎቱ እንደጨመረ ለማወቅ ጥናት አያስፈልግም። ብዛት ያላቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለመኖሪያነት እየተዘጋጁ ነው። ለዚህ ሁሉ ፍላጎት የሚመጥን ሥራ እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ በቀለ፡-** በዋናነት መሥመሮቹ አሉ። መስመሮቹን ለማሳደግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ተለዋጭ መስመሮችን አዘጋጅቶልናል። ለምሳሌ ኮዬ ፈጬ እና ቡልቡላን የመሳሰሉ ብዛት ያላቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ላይ ሥራ ተጀምሯል። ኮዬ ፈጬ ብቻውን ትልቅ ከተማ ነው። ባለው ኔትወርክ ውስጥ መግባት አይችልም። ለብቻው ከዛ ጋር አንድ በጣም ትልቅ ማከፋፈያ ጣቢያ ቆሞለታል። ስለዚህ ኃይል ከዛ ይወጣል።

በሌላ በኩል በየአካባቢው አጋዥ ትራንስፎርመር እየሠራን ነው። ፍላጎት ሲያድግ ትራንስፎርመር አብሮ ይጨምራል። ወደ ማከፋፈያ ጣቢያ የሚሔደው መስመር ከቻለ ቻለ፤ እርሱ እያለ የሚያድገውን ፍላጎት ብቻ ከስር ከስር እየጨመሩ መቀጠል ነው። ኔትወርኩ ላይ ቀጫጭን ሽቦዎች ከሆኑ በመደበኛነት የማሻሻል ወደ ወፍራም የመቀየር ሥራ ይሠራል። ከፍላጎት ዕድገቱ ጋር እኩል ለመሔድ እና ያለውን ለማሻሻል አሠራር ተዘርግቷል። ነገር ግን የአቅም ጉዳይ ችግር ነው።

**አዲስ ዘመን፡-አቅም ሲሉ የገንዘብ አቅም ማለትዎ ነው?**

**አቶ በቀለ፡-** ታዲያስ ገንዘብ ካለ ምን ችግር አለ። ሁሉንም መሥመር መለወጥ ይቻላል። በብድርም በምንም እያስለወጥን ያለነው ለዚሁ ነው። ገንዘቡ ካለ ከፍላጎቱ ጋር እኩል መሔድ አያዳግትም። ኅብረተሰቡ ምን ያህል እንደሚፈልግ ይነበባል፤ ፍላጎቱ ሲጨምር አጋዥ ትራንስፎርመር ከጎን ይቀመጣል። አሁን ኃይል አነሰ ሲባል፤ ኃይል አንሰጥም ይባላል። ምክንያቱም መሥመሩ መሸከም ስለማይችል ይፈነዳል በሚል ስጋት ነው። ነገር ግን አጋዥ ትራንስፎርመር እየተቀመጠ ከሆነ አዲስ አበባ ላይ ችግሩ እየተቃለለ ይሔዳል። ያለበለዚያ መስመር ላይ ችግር ሲኖር ኃይል ይቋረጣል። በዋናነት ኃይል የሚቋረጠው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ነው። መልሰው ቢለቁትም የቴክኒክ ጉዳይ ስለሆነ መልሶ መስመሩ አይሸከመውም በድጋሚ ይቋረጣል። በዚህ ጊዜ በደንብ ፈልጋችሁ ሥሩ ይባላል።

**አዲስ ዘመን፡- አዳዲስ የጋራ መኖሪያ ቤቶች አሉ። ለጋራ መኖሪያ ቤቶቹ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የምትሰጡበት አሠራራችሁ እንዴት ነው?**

**አቶ በቀለ፡-** እኛ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የምንሰጠው ሙሉ ለሙሉ ሥራቸው ለተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ነው። ልክ እንደየካ አባዶ በመሬት ውስጥ ለውስጥ (አንደርግራውንድ) ላይ መስመር እንዘረጋለን። ቤቶቹ ካለቁ ትራንስፎርመር አስገብተን ቆጣሪ እንለጥፋለን። የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ ብቻ የሚሠራ የፕሮጀክት ቢሮ አለ። እርሱ ከአዲስ አበባ ቤቶች ጋር በጋራ በማቀድ ምን ያህል እንደሚያስፈልግ ታውቆ ይሠራል።

አንዳንዴ የምንቸገረው የመንገድ ግንባታው ካላለቀ ነው። ለምሳሌ ኮዬ ፈጬ ላይ የተቸገርነው መንገዱ አላለቀም። ሰው ተቸግሯል፤ መሠረተ ልማቱ ባያልቅም ይገባል። ስለዚህ ጊዜያዊ መፍትሔ በማሰብ ከላይ መስመር እንዲዘረጋ እየተሠራ ነው። በተረፈ የቤቱ እና የመንገድ ግንባታው ከተጠናቀቀ መስመር ለመዘርጋትም ሆነ ቆጣሪ ለመለጠፍ ምንም ዓይነት ችግር የለብንም። አልፈን ተርፈን ከውጪ ትራንስፎርመር ተክለን ለመስጠት እና ሌላ ወጪ ለማውጣት ሁሉ ፈቅደን እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከኃይል መቆራረጥ ጋር ተያይዞ ብዙ ሰዎች የኃይል ማነስ ያጋጥማቸዋል። እንደውም ለእኛ በቂ ኃይል ሳይኖር ለሌላ አገር ተሸጠ የሚሉ ሀሜቶች አሉ። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ በቀለ፡-** እኛ ኃይል ጠይቀን ያጣንበት ጊዜ የለም። የኃይል ችግር ካለ በሀገር ደረጃ መነገሩ አይቀርም።

**አዲስ ዘመን፡- የጥሬ ዕቃ ችግር የለባችሁም? የውጪ ምንዛሪው ችግር እናንተን አልነካም?**

**አቶ በቀለ፡-** ከኬብል ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለማቃለል ግለሰቦች ኬብል እንዲገዙ አድርገናል። ትራንስፎርመር ደግሞ አምራቾች አሉ። የምንገዛው ከእነርሱ ነው። ኬብል አምራቾች ኢትዮጵያ ውስጥ በዝተዋል። ስለዚህ ይህን ያህል ችግር አለ ማለት አይቻልም። ምሰሶም ሆነ ቆጣሪ አለ። ጊዜያዊ ካልሆነ በቀር ከባድ የጥሬ ዕቃ ችግር የለም። ትራንስፎርመር የሚፈልግ ካለ ራሱ ይገዛል እኛ እንገጥማለን።

**አዲስ ዘመን፡- አሮጌ መስመር ማደስን በሚመለከት ምን ይላሉ? በእርግጥ እየታደሰ ነው?**

**አቶ በቀለ፡-** የ600 ኪሎ ሜትር እድሳት አልቆ ትልቅ እፎይታን ሰጥቷል። አሁን ደግሞ የ400 ኪሎ ሜትር ተጀምሯል። ወደ ፊት ይቀጥላል። ከስር ከስር በራስ አገዝ ቢሠራም፤ በሶስተኛ ወገን በተቋራጭ እየሠራን መሆኑ ትልቅ ውጤት እያስገኘ ነው። ራሳችን ካልሠራን ስንል ኅብረተሰቡ በብዛት በመንገላታቱ የኮንትራት ማኔጅመንት ቢሮ ለሦስተኛ ወገን ሥራውን እየሠጠ በፍጥነት በቀላሉ እየተሠራ ነው። እኛ ዕቃ እናቀርባለን ተቋራጩ ሥራውን ያጠናቅቃል።

**አዲስ ዘመን፡- ዕድሳቱ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ግራውንድ ታደርጉታላችሁ ወይንስ ምን ይሆናል?**

**አቶ በቀለ፡-** ግራውንድ መሠረተ ልማት ይፈልጋል። ከመስቀል አደባባይ እስከ ቦሌ ሙሉ አንደርግራውንድ ነበረ። ነገር ግን የመንገድ ሥራ አበላሸው፤ ስለዚህ ሙሉ ለሙሉ አወጣነው። የፈረንሳይ መንገድም በተመሳሳይ ፈርሷል። ስለዚህ ያለቀለት መንገድ ይፈልጋል። አሁን የተቸገርነው ይኸው ነው። አንደኛው መንገዶች ባለስልጣን ሥራውን ለሶስተኛ ወገን ይሰጣል። እነርሱ ሳያማክሩን ወደ መንገድ ቁፋሮ ሲገቡ መስመር ይቋረጣል። የሆነ ቦታ ይፈነዳል። በትክክል የተበላሸበትን ማወቅ ራሱ መከራ ይሆናል። መከራችንን የበላነው በዚህ ነው። በጥገና ምክንያት ሰዎች ይሰቃያሉ።

**አዲስ ዘመን፡-የተለያዩ የመሠረተ ልማት አውታሮችን የሚያቀናጅ ተቋም ተቋቁሞ ነበር። በሥራ ላይ የምትሠሩት በቅንጅቱ መሠረት ነው?**

**አቶ በቀለ፡-** ተቀናጅቶ ለመሥራት ይሞከራል፤ ነገር ግን ችግሩ መንገዶች ለሦስተኛ ወገን ሲሰጡ ችግር ይፈጠራል።

**አዲስ ዘመን፡- የኤሌክትሪክ አገልግሎት የዋጋ ማስተካከያ ተደርጓል። ሠራተኛው ምን ተጠቀመ? ደመወዝ ጥቅማጥቅም እና በተለይ በሥራ ላይ**



**አደጋ ሲደርስ የሚሰጠውን ካሳ በሚመለከት ምን ለውጥ መጣ?**

**አቶ በቀለ፡-** ማስተካከያው የተደረገው ከግዢው ጋር ተያይዞ ነው። የጥሬ ዕቃ ዋጋ ጨምሯል። ለአራት ተከፋፍሎ ታሪፉ ጭማሪ ተደርጓል። አሁን አልቋል። የአገልግሎት አሰጣጣችንን እና የግዢ ሥርዓታችንን እኩል ለማድረግ ብቻ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የተቋሙ ሠራተኞች ደመወዝ በሚመለከት ምን ለውጥ አለ?**

**አቶ በቀለ፡-** ተቋሙ ሠራተኛ ማኅበር አለው። ማኅበሩ ይደራደራል። ያለውን የኑሮ ውድነት ማዕከል በማድረግ በየዓመቱ ጭማሪ ወይም ማስተካከያ አለ። ጉዳቱ ላይ ኢንሹራንስ አለ። ነገር ግን ቀድሞ መጠንቀቅ ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው። ራሱን የቻለ ክፍል ተከፍቷል። በቸልተኝነት አደጋ እንዳይደርስ ዕቃዎችን የሚያሟላ ክፍል አለ። ነገር ግን በማስተማር እና በመከላከል ካልሆነ ውጤቱ ብዙ አይሆንም። መስመር ሲበጠስ ስለማይታይ አደጋ ይደርሳል፤ ምክንያቱም እሳቱ ሽቦ ላይ አይታይም ሲነካ ይገድላል። ዋናው ነገር ጥንቃቄው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚሉት ካለ ዕድሉን ልስጥዎት።**

**አቶ በቀለ፡-** ተቋሙ ሕዝቡ ያለውን ፍላጎት ለሚሟላት ዕቅድ አለው። በዕቅዱ መሠረት እየሠራን ነው። ሌላው ፍጆታቸውን በጊዜ የማይከፍሉ በአግባቡ ይክፈሉ። ምክንያቱም በክፍያ ምክንያት አገልግሎት ማቋረጥ ለተቋማችንም ለተገልጋዩም ኪሳራ ነው። ለፍጆታው ቶሎ በተገቢው ጊዜ ከተከፈለ አገልግሎቱ የበለጠ የተቀላጠፈ ይሆናል። ሌላው በየአካባቢው የኃይል መዋዠቅ የሚያጋጥመው በኃይል ስርቆት ምክንያት ነው። ስለዚህ እንጀራ ቤቶች እና ብረት መበየጃዎች በመሳሰሉት የሥራ ቦታዎች የኤሌክትሪክ ስርቆት አለ። እዚህ ላይ ኅብረተሰቡ መጠቆም አለበት።

**አዲስ ዘመን፡-ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ በቀለ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# መንግሥታት ሲለዋወጡ በበትራቸው የሚቆስለው ተቋም

**የመጀመሪያው ስህተት፤ የኋለኛው እብደት!**

የሀገሬ የመንግሥታት ሽግግር ዋና መለያው ነባር ተቋማትን አፈራርሶና አጥፍቶ “አዲስ” በሚሰኙ መዋቅሮች ማውገርገር ስለመሆኑ ታሪካችን የሚመሰክርልን “እያነባ” ጭምር ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት እጅግ ደክሞበትና ዋጋ ከፍሎበት ያቋቋማቸውን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች የወታደራዊው የደርግ ሥርዓት ገና “በትረ ሥልጣኑን” በጨበጠ ማግሥት እንደምን እየናደ ወደ ፍርስራሽነት በመለወጥ ቅርስና ውርስ አልባ እንዳደረገን በብዙ ማስረጃዎች ማመላከት ይቻላል።

“በፊውዳሊዝም ሥርዓት ላይ ሶሻሊስት ኢትዮጵያን እንገነባለን!” በሚለው የርዕዮተ ዓለም የጉሽ ገፈት ፍልስፍው ሰክሮ ያሳከረን የደርግ ሥርዓት ሀገሬን ሀገር ያሰኟትን በርካታ ተቋማዊ እሴቶች እንክትክታቸውን ያወጣው ትዕቢትና እብሪት አሳብዶትና በንጉሣዊ አስተዳደር ጥላቻ ሰክሮ እንጂ በርግጥም በቂና አሳማኝ ምክንያት ኖሮት አልነበረም።

“ግፍ ያናወጠው ባሕር፤ ድንጋይ አንሳፎ ላባ ያሰጥማል” እንዲሉ፤ ወታደራዊው የደርግ ሥርዓትም እንዲሁ ዕድል ፊት ነስታው የወር ተራ ጀንበሩ ስታዘቀዝቅ “አጉራህ ጠናኝ” በማለት ተሸንፎ መንበሩን ለተረኛውና ከጫካ እያገሳ ለወጣው ወያኔ/ኢህአዴግ ያስረከበው በራሱ ስህተቶች እጁን ለካቴና አሳልፎ በመስጠት ነበር። አዲስ መጭው የወያኔ ሥርዓትም እንዲሁ ልክ እንደ ቀዳሚው የደርግ ሥርዓት በመጀመሪያ የወሰደው ርምጃ መንግሥታዊ ተቋማትን አፈራርሶ ቀብራቸውን ማስፈጸም ነበር።

በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜና ዐውድ ሲፈቅድልን ተመልሰን ብዙ ጉዳዮች እንደምንዳስስ ቃል በመግባት ለዛሬው ርዕሰ ጉዳይ ምክንያት ሆኖ ሃሳቡን ያጫረብን በቅርቡ የታተመ አንድ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ርዕስ “የመረጃ ደኅንነት ሙያ እና የኢትዮጵያ ገፅታው፤ ትውስታና ትንታኔ ከ1965 - 1983 ዓ.ም” የሚል ሲሆን ደራሲው ደግሞ በላይ ገብረ ጻድቅ የሚባሉ ኅምቱ ምሁርና የሀገራችንን የደኅንነት መሥሪያ ቤት ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ የሀገር ባለውለታ ናቸው።

ባሕር ማዶኞች ከፈረሱ አፍ “straight from the horse’s mouth” እንዲሉ ደራሲው ያበረከቱልን ይህ መጽሐፍ ከራሳቸው ሙያና ታሪክ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ስለሆነ ስለማንነታቸው በአጭሩ ዘርዘር አድርጎ ማስተዋወቁ መጽሐፉን በጉጉት እንድናነብ ይገፋፋናል። ይህ ጸሐፊም ደራሲውን ከልጅነቱ ጀምሮ በሚገባ ስለሚያውቃቸውና መጽሐፉ በተመረቀበት ዕለትም በይዘቱ ላይ አጭር የዳሰሳ ጥናት አቅርቦ ስለነበር ማስተዋወቂያው ከመጻሕፍቱ የተወሰደ ብቻ ሳይሆን የረጂም ዓመታት ቅርበት ምስክርነትም የታከለበት ነው።

ደራሲው በላይ ገ/ጻድቅ አባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ከሚባለው ዝነኛ ተቋም በ1965 ዓ.ም በምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ተመርቀው በቀጥታ ሥራ የጀመሩት በንጉሡ ነገሥቱ የመረጃ ተቋም ይባል በነበረው የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ ሲሆን በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ ተመድበውም አገልግለዋል።

ደርግ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላም ከመስከረም 1967 - 1983 ዓ.ም በበረራ ደህንነት ጥበቃ፣ በተለያዩ የመረጃ ሥራዎች፣ በሀገርና ሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ የሚኒስትሩ ልዩ ረዳትና በኋላም ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዛውረው በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ አንደኛ ጸሐፊ፣ በምሥራቅ ጀርመንና በእስራኤል ኤምባሲዎቻችን ውስጥ አማካሪና ላይዘን ኦፊሰር በመሆን ሀገራቸውን እስከ ሰኔ 1983 ዓ.ም በታማኝነት አገልግለው በመጨረሻም በሕወሓቱ የደኅንነት ኃላፊ ከሥራ በመታገዳቸው ላለፉት 30 ዓመታት ያህል በስደት የቆዩት በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ ነው።

**አሸማቆ ኖሮ ተሸማቆ የሚያልፈው ተቋም፤**

ምክንያታዊነቱን ለማብራራት ቢያዳግትም በኢትዮጵያ የተቋማት ታሪክ ውስጥ ተፈርቶና አሸቆጥቁጦ ኖሮ፤ መንግሥታት በተለዋወጡ ቁጥር ዐይንህን ለአፈር ከሚባሉ ተቋማት መካከል አንዱ የደኅንነት መሥሪያ ቤት ነው። ስያሜው ከሥርዓት ሥርዓት ሲለዋወጥ ቢኖርም ሕዝቡ በነቂስ በሚስማማበት የተለመደ ስሙ “የደኅንነት ተቋም” እያልን መጥራቱን መርጠናል።

የደኅንነት ተቋም እንኳንስ ለእኛ መሰሉ በብዙ ጠላቶች ተከቦ ጥርስ ለገባ ሀገር ቀርቶ ለማንኛውም ሉዓላዊና የተረጋጋ ለሚመስል ሀገርም ቢሆን የእስትንፋስ ያህል እጅግ አስፈላጊ ነው። ያለ ሕግ ሥርዓት፣ ያለ መከላከያ ሠራዊትና ያለ ጠንካራ የደኅነት ተቋም አንድ ሀገር፣ ሀገር ተብሎ ተከብሮ ሊጠራ ከቶውንም አይችልም። በተለይም የደኅነቱ ተቋም ደካማና ልፍስፍስ ከሆነ የሀገር ገመና ተራቁቶ ለመዋረድ ቅርብና ቀላል ይሆናል። በትንሽ በትልቁ ጡንቻቸውንና ጉልበታቸውን እያሳዩ ሕዝብን ለማሸበርና ሰላምን ለማናጋት እንቅልፍ ለሚያጡ የውጭና የውስጥ ጠላቶችም የሠርግና የምላሽ ያህል የሚያስፈንድቅ ነው። መከላከያ ሠራዊት የሀገርን ድንበርና ሉዓላዊነት ለማስከበር አደራውን በጫንቃው ላይ የተሸከመውን ያህል የደኅንነቱ ተቋም ደግሞ ተግቶ ኃላፊነቱን የሚወጣው “አራት ዐይናማ በረኛ” በመሆን ነው።

ያለመታደል ሆኖ በዚህ ሰሞን እንኳን ሕዝቡን እምባ ባራጩ የአሸባሪ ቡድኖች ተደጋጋሚ ድርጊቶች የተማረረው ሕዝብ “ለመሆኑ በየአካባቢዎቹ የተፈጸሙት የወገን ጭፍጨፋዎች፣ የንብረት ውድመቶችና መፈናቀሎች ሲፈጸም የደኅንነት ተቋሙ ምን ይሠራ ነበር?” እየተባለ በብዙዎች ሲጠየቅ መሰንበቱ የተቋሙን እጅግ አስፈላጊነት የሚጠቁም ነው። እርግጥ ነው አገልግሎቱ እጅግ የላቀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዛሬም ቢሆን ሕዝቡ በደኅንነት መ/ቤቱ ላይ ያለው አመለካከት ሙሉ ለሙሉ ከፍርሃት ቆፈን የተላቀቀ ነው ለማለት ያዳግታል። መ/ቤቱም ቢሆን ወደ ሕዝብ ልብ ውስጥ ጠልቆ ገብቶ ለመወደድና በአለኝታነቱ እንዲከበር ተገቢው ሥራ ተሰርቷል ለማለት ያዳግታል።

ለማንኛውም በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን ታሪክ ረጂም ዕድሜ የሚቆጠርለት የደኅንነት ሙያ መንግሥታዊ ሥርዓቶች በተፈራረቁ ቁጥር በፍርሃትና በጥርጣሬ ስለሚታይ የአዲስ መጭው ሥርዓት ዱላ ቀድሞ የሚያርፈው በተቋሙና በባለሙያዎቹ ላይ ነው። ይህን መሰሉ የረዥም ዘመናት ገድልና ታሪኩ በተጠቀሰው የደራሲ በላይ ገ/ጻድቅ መጽሐፍ ውስጥ በሚገባ ስለተተረከ የአስተማሪነቱ ዋጋ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

ደራሲው ለሁለት ዓመት ያህል ያገለገሉበትን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የመረጃ ተቋማት የገለጹት፤ “የአገሪቱን ሰላምና ጸጥታ ከማስጠበቅ አኳያ ከፍተኛ ብቃት እንደነበራቸው ለመናገር ብዙም ምስክር አያሻም። ተቋማቱን ለማቋቋም የሚያስፈልጋቸውን መዋቅራዊ ድጋፍና የሙያተኞች ሥልጠና ያገኙ የነበረው ትናንትናም ሆነ ዛሬ በዓለማችን ውስጥ ታዋቂ በሆኑት በአሜሪካዊያንና በእስራኤላዊያን ተቋማት ነበር። ” በማለት ነው።

በዚህም ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር የተነሳ በንጉሡ ዘመን በይፋ የሚታወቁት የመከላከያ መረጃ ተቋማት፡- የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ፣ የፖሊስ ሠራዊት ልዩ ቅርንጫፎችና ኤታማዦር በመባል ይታወቅ የነበረው የመገናኛ መረጃ ማዕከል በጥቅሉ ዘመኑ ባፈራቸው ብቁ ባለሙያዎችና ወጣት ወጣት ሙያተኞች የተገነቡ ስለነበሩና በአመራር ላይ የነበሩ ከፍተኛ ባለሥልጣናቱም በእውቀትና በልምድ አንቱ የመሰኘት አክብሮት የተጎናጸፉ ስለነበሩ ተቋማቱ በአህጉር ደረጃ ሳይቀር ጠንካራ እንደነበሩ በዝርዝርና በተጨባጭ የኦፕሬሽን ማስረጃዎች ለማመለከት ሞክረዋል።

በአንጻሩ “ንጉሣዊ አገዛዙን የተካው የደርግ መንግሥት በአብዮቱ መባቻ ላይ በአገሪቱ የነበሩትን የመረጃ ተቋማት እንደ ንጉሡ ንብረት አድርጎ ከሕዝብ ጋር ለመተዋወቂያነት እንደተጠቀመበት ታሪኩን በዝርዝር አስፍረዋል። ገና ሙሉ ለሙሉ ሥልጣኑ ላይ ከመንሰራፋቱ አስቀድሞም ተቋማቱን በጅምላ ፍረጃ ፀረ-ሕዝብና ሀገር፣ አፋኝ፣ ጨቋኝ፣ የንጉሡን ሥልጣን ብቻ ለመጠበቅ እንደተቋቋሙ በመቁጠር የሕዝብን ፍቅርና አመኔታ መሸመቻ አድርጎት ነበር” - ይሉናል። ከዚህም አልፎ ተርፎ ነባርና በእውቀታቸውና በልምዳቸው የተከበሩትን መሪዎቹን በመረሸን፣ በርካታ ነባር ባለሙያዎቹም ሀገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ እንዳደረገ ማስረጃው በዝርዝር ቀርቧል።

እያደረ ግን በሥርዓቶቹ ሽግግር መካከል ዛሬም ድረስ ከታሪካዊ ጠላትነት ሊለዝቡ ያልቻሉ አንዳንድ የቅርብና የሩቅ መንግሥታትና በሀገር ውስጥ የመገንጠል ዓላማ አንግበው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖችና ገና ከእትብቱ ተላቆ ድክ ድክ ማለት ያልተጀመረው የወያኔ ቡድን በነባሩ ባለሙያዎች የረቀቀ ክትትል ተልእኳቸው መክሸፍ መጀመሩን የተረዱት አንዳንድ የአዲሱ የደርግ መንግሥት ሹማምንት ነባሮቹን የደኅንነት ባለሙያዎች በተመለከተ፤ “እነዚህ ሰዎች እኛ ስንለው እንደከረምነው ሳይሆን ሥራቸው የንጉሡን አልጋ ከመጠበቅ በላይ ነው። ” ብለው ምስክርነት መስጠታቸውም ተረጋግጧል።

ከደርግ በኋላ ጸጉሩን አጎፍሮ ከጫካ የወጣው የወያኔ/ኢህአዴግ “መንግሥት” ሥልጣን በያዘ ወር ባለሞላ ጊዜ ውስጥ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ የደኅንነቱን ተቋም እንዳለ ማፍረስ፣ ኃላፊዎቹንና ሠራተኞቹን ማሳደድ፣ ማሰርና መግደል ነበር። በዚሁ ጭፍን ድንብር የበቀል ውሳኔም ሀገሪቱ መከራ ላይ ለመውደቅ፣ ሕዝቡም የስቅቅ ኑሮ እየኖረ ለማንባት ጊዜ አልፈጀበትም።

ደራሲው እጅግ ከረቀቁ ታሪካዊና ተጠቃሽ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት የኦፕሬሽን ስኬቶች ጋር እያዋዙና እያስደመሙ የዘረዘሯቸው ታሪኮች በእጅጉ የሚያስደንቁና ለተመራማሪዎችም እንደ አንድ ከፍተኛ ሰነድ የሚያገለግሉ ናቸው። መጽሐፉ ምናልባትም በዚህ ዘርፍ በቀዳሚነት የሚጠቀስ የመጀመሪያ ሥራ ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚችል ይታመናል። ከዚህ በኋላም ሌሎች ጸሐፍት የደራሲውን ፈለግ ተከትለው በርካታ መሰል መጻሕፍትን ለንባብ እንደሚያበቁ ይጠበቃል።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በንባቡ መካከል እጅግ የተመሰጠባቸውና የተዝናናባቸው በርካታ እውቀቶች፣ መረጃዎችና ፈገግ የሚያስደርጉ ታሪኮች የተጠቀሱ ቢሆንም መጽሐፉ እንዲነበብ የሚያበረታቱትንና እንደ “ዲዘርት” የሚያገለግሉ ጥቂት ታሪኮችን ከመጽሐፉ ውስጥ ነቅሰን እንጠቁም። እንደማዝናኛነት ከጠቀሷቸው የይባላል ታሪኮች አንዱ ስለ ንጉሡ የተገለጸው በእጅጉ ፈገግ የሚያስደርግ ነው።

“ጃንሆይ ይደርሷቸው ከነበሩት ዕለታዊ መረጃዎች መካከል የሚያስደስቷቸው፣ የሚያዝናኗቸውና በጉጉት ከሚጠብቋቸው መካከል ሚኒስትሮቻቸውና የጦር አዛዦቻቸው በየጊዜው እርስ በእርሳቸውና ከሴቶች ጋር በስልክ ያድርጉ የነበረው ጭውውት፤ ዋናዎቹና የሚናፍቋቸው እንደነበሩ በሃሜት መልክ ይነገር ነበር። አልፎ አልፎም በድምጽ ተቀድተው የሚቀርቡላቸውን መረጃዎች ሲሰሙ የማያቋርጥ ሳቅ ይስቁ ነበር። ” በማለት ፈገግ የሚያሰኙ መሰል “እውነታዎችን” በየመሃል ጣል ጣል ያደርጋሉ።

“ድብቁ ሰው” በመባል ይታወቁና ይፈሩ የበሩትን የደርግን የደኅንነት መ/ቤት ሚኒስትር ሌ/ኮ ተስፋዬ ወልደ ሥላሴን፤ ታሪኮቻቸውን ጽፈው እንዳስነበቡን እንደ ብዙዎቹ የሚኒስትሩ የቅርብ ጓደኞች በደላቸውንና ፈጸመዋቸዋል የሚሉትን ግፎች ብቻ እየዘረዘሩ “የጦስ ዶሮ” ሊያደርጓቸው አልሞከሩም። ይልቁንስ እንደ ቅርብ አለቃና ልዩ ረዳታቸው ደራሲ በላይ ገ/ጻድቅ የሰጡት ምስክርነት በእጅጉ የሚያስመሰግናቸው ነው።

“ኮ/ሌ ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ ጨዋ፣ ሰውን በባሕርይውና በችሎታው ብቻ የሚመዝኑ፣ ማሥራት የሚችሉና የሚያበረታቱ፣ ብዙ የሚያደምጡ፣ ችኩል ያልሆኑ፣ ሰዎችን የሚያቀርቡ እንጂ የማይገፈትሩ፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ የበታቾቻቸውን በትዕግሥት የሚያደምጡ፣ መመሪያዎችን ሲሰጡ የተለየ ሃሳብ ሊኖር ይችላል በሚል የሚጠይቁ አዛዥ እንደነበሩ ጸሐፊው ያስታውሰል... በልምድም ሆነ በሙያ በሚፈለገው ትምህርት ከአንዳንዶች በስተቀር ኮ/ል ተስፋዬ የተሻሉ ነበሩ። ” በማለት የግላቸውን ምስክርነት ከሰጡ በኋላ ድካማቸውን የገለጹትም በጨዋነት ነበር። እንዲህ በማለት፤ “እርግጥ ነው የኮ/ል መንግሥቱን ዘለፋ ለመርሳት አልኮልና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነገሮችን ያዘወትሩ ነበር የሚል ሀሜትም ይሰማባቸው ነበር። ” ይህ ገለጻ በደልንና ጥፋትን ብቻ ከማጉላት ይልቅ የሰዎችን ጠንካራ ጎን ለመገለትም ኅሊናን ማድመጥ እንደሚገባ ጥሩ ማሳያ ነው።

ደራሲው እጅግ ጠቃሚ የሆኑ እውቀቶችን፣ መረጃዎችን እያዋዙ በማቅረብ ለአንባቢያን እንደሚጠነቀቁ በመጽሐፉ ውስጥ በጉልህ ይስተዋላል። በየሥርዓተ መንግሥታቱ በደኅንነቱ ተቋምና በሠራተኞቹ አማካይነት ስህተት በፍጹም አልተፈጸመም፣ መሪዎቹም “ከደሙ ንጹሕ ነበሩ” ለማለት ሳይሆን ከድክመት ዝርዝር ጋር በሚቀራረብ መጠን ጥንካሬንም ማሳየቱ መልካም መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ስለዚህም ይህ መጽሐፉ አንዴ ብቻ ተነቦ የሚቀመጥ ሳይሆን ብዙ ታሪኮችና እውነቶች እየተመዘዙለት የትናንቷንና የዛሬዋን ኢትዮጵያ በሚገባ ንጽጽር ማሳየት የሚችል ስለሆነ ደራሲውን በማመስገን አንባቢያን መጽሐፉን እንዲያነቡ ጸሐፊው ያበረታታል። ሰላም ይሁን።

# የአሽከርካሪዎችን ሥራ እየተገዳደረ የመጣው የነዳጅ ግብይት ሠልፍ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ለነዳጅ መቅዳት የሚደረገው ሰልፍ ወርሐዊ ትዕይነት ሆኖ ቆይቷል። በየወሩ የነዳጅ ክለሳ ይደረጋል በሚል ነዳጅ ለመቅዳት የማይሰለፍ ተሽከርካሪ አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ችግሩ ከፍቷል። በአዲስ አበባ ተሽከርካሪዎች ረጃጅም ሰልፎችን ለሰዓታት መሰለፍ ግድ ሆኖባቸዋል። ከማለዳ አንስቶ ምሽት ድረስ ከባጃጅ አንስቶ እስከ ከባድ መኪና ድረስ ለረጅም ሰዓት ይሰለፋሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ ሁሉም ስፍራ በሚገኙ ነዳጅ ማደያዎች ረጃጅም የመኪና ሰልፎች በየቀኑ እየታዩ ናቸው። የሰሞን ወይም የወር ሳይሆን የዓመት ቀለባቸውን ሊሸምቱ የተሰለፉ በሚመስል መልኩ ነው መኪኖች ተሰልፈው የሚታዩት።

ሰልፉ ሁሉንም ዓይነት ተሽከርካሪዎች ያካተተ መሆኑ ደግሞ የሰሞኑን የነዳጅ ወረፋ የተለየ ያደርገዋል። መጀመሪያ ላይ በአብዛኛው ይሰለፉ የነበሩት ናፍጣ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ነበሩ። ወደ ሀገራችን ከሚገባው ነዳጅ 60 በመቶው ናፍጣ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። የናፍጣ አቅርቦት ሲስተጓጎል ምን ያህል ተሽከርካሪዎችና ሕዝብ ለችግር እንደሚዳረግ ከዚህ በመነሳት መገመት አይከብድም። አሁን አሁን ደግሞ የቤንዚን ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች ተራ ጥበቃውን በብዛት ተቀላቅለውታል። ነዳጅ የጨረሰ ማደያ ጭር ይል ይሆናል እንጂ የተቀሩት ሙሉውን ቀን በተሽከርካሪ ሰልፍ ተጨናንቀዋል።

ተሽከርካሪዎች ረጃጅም ሰልፎችን ይዘው በነዳጅ ማደያዎች ዙሪያ የመኮልኮላቸው ሚስጥር በናፍጣና በቤንዚል እጥረት ቢሆንም፣ እጥረቱ የተከሰተው ሰው ሠራሽ በሆኑ ችግሮች መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

በመዲናዋ በሁሉም አቅጣጫዎች ሳምንትን የዘለቀው የነዳጅ እጥረት አሽከርካሪዎች ዕለታዊ ሥራቸውን ማቀላጠፍ እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው እየገለጹ ናቸው። ለሥራ ሊውል የሚገባውን ረጅም ጊዜ በነዳጅ ፍለጋና በወረፋ ጥበቃ ለማሳለፍ መገደዳቸውን ያነጋገርናቸው አሽከርካሪዎች ይጠቁማሉ።

ከሁለትና ሶስት ሳምንት አስቀድሞ ናፍጣ መጥፋቱን አሽከርካሪዎቹ ያስታውሳሉ፤ አሁን ደግሞ በአብዛኞቹ የነዳጅ ማደያዎች ውስጥ የቤንዚን እጥረት መከሰቱን ይጠቁማሉ። ቤንዚን አለ ወደተባለበት አካባቢ ሲዘዋወሩ እንደዋሉና አለ በተባለበት ቦታም አሰልቺውን ወረፋ ለመጠበቅ መገደዳቸውን ጠቅሰው፣ ይህም በሥራቸው ላይ የበረታ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ነው የሚናገሩት።

በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች ቤንዚን ፍለጋ ተዘዋውረው አራት ኪሎ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አጠገብ ከሚገኘው ነዳጅ ማደያ መገኘታቸውን ከገለጹልን አሽከርካሪዎች መካከል ወጣት ሄኖክ ግርማ አንዱ ነው።

ከነዳጅ ማደያው በቅርብ ርቀት ተሰልፎ ተራውን እየተጠባበቀ ያገኘነው ሄኖክ፤ የራይድ አሽከርካሪ ነው። ከሰሞኑ በነዳጅ ላይ እየታየ ያለው ችግር በእጅጉ እንዳሳሰበውና ስጋት ላይ እንደጣለው አምርሮ ይናገራል።

ሄኖክ ችግሩ መንግሥት ነዳጅ ላይ ሲያደርግ የነበረውን ድጎማ ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሊያነሳ መሆኑን ተከትሎ ሕገወጦች የፈጠሩት ነው። ችግሩ በተለይም በራይድ አሽከርካሪዎች ላይ ሊብስ እንደሚችል ያለውን ስጋት ገልጾልናል። ራይድ በቀን ገቢ ተቀብሎ የሚሠራ እንደመሆኑ ነዳጅ ለመቅዳት ብቻ በቀን ከአራት ሰዓት በላይ መቆም ሥራውን ፈታኝ ያደርገዋል ይላል።

ሁሉም ነገር ከነዳጅ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመጥቀስም ሄኖክ የኑሮ ውድነቱም ይበልጥ እንዳይባባስ ስጋት አድሮበታል፤ ድጎማው ይነሳል በሚል ይህን ያህል እጥረት ከታየ ድጎማው ሲነሳ ደግሞ ችግሩ ምን ያህል ሊባባስ እንደሚችል መገመት ቀላል ነው ሲል ያመለክታል። የሚመለከተው የመንግሥት አካል ያለውን ችግር ከመረዳት ባለፈ የእኛንም እንግልት በልኩ ሊያጤንና አቅርቦቱን በማስተካከል መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው ብሏል።



**ነዳጅ ለመቅዳት በየማደያው ለሰዓታት መሰለፍ የግድ ሆኗል**

ለአራት ሰዓታት ተሰልፈው ከማደያው ግቢ የደረሱት ሌላው አሽከርካሪ ፍቃዱ ከፈተውም የወጣት ሄኖክን ሀሳብ የሚያጠናክር ሀሳብ ይሰነዝራሉ። አቶ ፍቃዱ፤ ቤንዚን ለመቅዳት ለስድስት ሰዓታት ተሰልፈዋል፤ ይህም ከብዙ ሥራቸው ያስተጓጎላቸው መሆኑን ተናግረዋል።ገና ድጎማው ሳይነሳ በዚህ ደረጃ ገበያው ከተረበሸ ድጎማ ሲነሳ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በማሰብ ያላቸውን ስጋት ይገልጻሉ።

አቶ ፍቃዱ ችግሩን ለመፍታት መሠራት እንዳለበት አስረድተዋል። መንግሥት በነዳጅ ላይ ሲያደርግ የነበረውን ድጎማ ሊያነሳ ነው ከሚል ስግብግበነት የመጣ ስለመሆኑ መረጃ ያላቸው እንደሆነ ያነሱት አቶ ፍቃዱ፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ማደያዎቹ በፍጥነት እየቀዱ አለመሆኑን እና መብራት ጠፋ እየተባለም በእጅጉ መጉላላት እንደሚስተዋል ነው ያመለከቱት።

በነዳጅ ግብይት ላይ ፊቱንም በተለይ ወር በቀረበ ቁጥር የዋጋ ክለሳ ይደረጋል በሚል ሕገወጦች አሉታዊ ተጽእኖ ሲያሳደሩ ኖረዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግሥት በነዳጅ ላይ ሲያደርግ የቆየውን ድጎማ ከመጪው ሐምሌ ጀምሮ በሂደት እንደሚያነሳ ማሳወቁን ለእዚህም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተከትሎ ሕገወጦች የነዳጅ ገበያውን እየረበሹት ይገኛሉ። በነዳጅ አመላላሽ ቦቴዎች፣ በነዳጅ ማደያዎች እንዲሁም በአንዳንድ አሽከርካሪዎች ጭምር በነዳጅ ላይ ሕገወጥ ተግባር እየተፈጸመ ነው።

ነዳጅ አመላላሽ ቦቴዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ነዳጁን ማደያዎች ማድረስ ሲገባቸው በየቦታው እያቆሙ ዋጋ እስከሚከለስ ይጠብቃሉ። አንዳንዶቹም ነዳጁን እስከ መሸጥ ይደርሳሉ። በጎረቤት ሀገሮች የነዳጅ ዋጋ በዓለም ገበያ ዋጋ የሚሸጥ መሆኑን ተከትሎ ዋጋው ውድ መሆኑንም ቦቴ አሽከርካሪዎች፣ ባለማደያዎች እና ሕገወጦች ነዳጁን ወደ ጎረቤት ሀገር በኮንትሮባንድ መልክ እያስወጡ ናቸው። አንዳንድ አሽከርካሪዎች ደግሞ የነዳጅ ዋጋ ይወደዳል ወይም የነዳጅ እጥረት ይከሰታል በሚል ነዳጅ በበርሜልና በመሳሰሉት ይደብቃሉ። ይህ ሁሉ የነዳጅ ግብይቱን ችግር ውስጥ ከቶታል።

መንግስት በነዳጅ ግብይቱ ላይ እየተፈጸመ ያለው ሕገወጥ ድርጊት ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወሰድ ቆይቷል፤ ይሁንና ችግር እየተባባሰ እንጂ እየተወገደ አልመጣም። አሁን ከአንድ ሳምንት ለተሻገረ ጊዜ የነዳጅ ግብይቱ ቀውስ ውስጥ መግባቱ የሚያመለክተውም እርምጃው ውጤት እያመጣ አለመሆኑን ነው።

የነዳጅ ድጎማ መነሳት የሚጀመርበትን መጪውን ሐምሌ ወር ታሳቢ በማድረግ ለሕገወጥ ድርጊት ያቆበቆቡ አካላት ታይተዋል። በርካታ ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች የጫኑትን ነዳጅ በወቅቱ ማደያዎች ማድረስ ሲገባቸው በየመንገዱ እየተጎተቱ፣ እየተደበቁ ናቸው። ይህ ነው በአሁኑ ወቅት ለተፈጠረው የነዳጅ እጥረት ምክንያት የሆነው። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የነዳጅ እጥረት የተከሰተው በዚህ ምክንያት ነው። ይህም በሀገሪቱ ያለው የነዳጅ ግብይት ጤናማ እንዳልሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ይህን ተከትሎ መንግሥት አሁን መረር ወዳለ እርምጃ እርምጃ እየገባ ነው። በተለያዩ አካባቢዎች በእዚህ ሕገወጥ ግብይት ውስጥ የተገኙ ቦቴዎች እና ማደያዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ተጀምሯል። እርምጃው እንዳለፉት ጊዚያት በማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ ብቻ የሚታለፍ አይደለም። የቁጥጥርና ክትትል ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በተደረገው የቁጥጥር ሥራም ሰሞኑን 200 የሚደርሱ ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች ከጅቡቲ ተነስተው ወደ አዲስ አበባና ወደ ተለያዩ መዳረሻ ቦታዎቻቸው መድረስ ሲገባቸው ከመንገድ ቀርተው በየጥጋጥጉ መደበቃቸው ታውቋል። ከቀናት በፊት እንዲሁም ከሳምንት ቀድመው በየቦታቸው መድረስ ይገባቸው የነበሩት ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች የጫኑትን ነዳጅ በተላኩበት ማደያ ደርሰው እንዲያራግፉ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ተግባራዊ በማያደርጉት ላይም መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ከሰሞኑ አስገንዝቧል።

የነዳጅ እና ኢነርጂ ቁጥጥር ባለስልጣን ነዳጅ ለመቅዳት በማደያዎች የሚታዩ ረጃጅም ሰልፎችን ለማስቀረት በቀን ከ10 ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ ካለፈው እሁድ ጀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑን ማስታወቁን ፋና ብሮድካስቲንግ ዘገባ ያመለክታል።

በአቅርቦት በኩል ክፍተት እንዳይኖርም ቀድሞ በቀን ይቀርብ ከነበረው 9 ሚሊዮን ሊትር ወደ 10 ሚሊዮን ሊትር ነዳጅ ማሳደጉን የባለስልጣኑ የነዳጅ ስታንዳርድ ጥራት ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ቱሉ ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ነዳጅ የጫኑ ቦቴ ተሽከርካሪዎች መንገድ ላይ መዘግየት እንዳይፈጠር እና ስርጭቱ ላይ ችግር እንዳይኖር ለማድረግ ኮሚቴ ተዋቅሮ በዘላቂነት ለመፍታት እየተሠራ ነው። ባለፈው ሳምንት እንደ ሀገር 200 ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች ከጂቡቲ ተነስተው 18ቱ ሞጆ ወደብ መድረሳቸውን እና የተቀሩት ላይ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንደተወሰዳባቸው አቶ ለሜሳ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 8 ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች የተቀመጠላቸውን ቀነ ገደብ ባለማክበራቸው ምክንያት ነዳጁን መውረሱን አቶ ለሜሳም ጠቅሰው፣ ሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ እርምጃ እየወሰዱ መሆኑን ተናግረዋል። ትናንት የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ደግሞ በሌሎች ሁለት ቦቴዎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተፈጽሟል።

የችግሩን መጠን በፍጥነት ለመቀነስ እንዲያስችል እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው÷ በተደረገው ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ባለፈው እሁድ 39 ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች አዲስ አበባ መድረሳቸውን ጠቁመዋል።

በሌላ የባለስልጣኑ መረጃ በሀገሪቱ የነዳጅ አቅርቦት ችግር የለም። ቢኖር እንኳ ከመጠባበቂያ ክምችት ማውጣት ይቻላል። የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አሕመድ ሰይድ ለፋና ብሮድካስት እንዳሉት፤ አስፈላጊው ነዳጅ ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ እየተደረገ ነው። ችግሩ ያለው ከጅቡቲ የሚመጣውን ነዳጅ የሚፈለገው ቦታ አለማድረስ ላይ ነው።በነዳጅ አመላላሽ ቦቴዎች በኩል የመደበቅና የመጎተት ነገር ይታያል።

በነዳጅ ማጓጓዝና ግብይት ላይ የሚሠራ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየሠራ መሆኑን አቶ አሕመድ ጠቅሰው፣ በሚደበቁና በሚዘገዩ ቦቴዎች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። እርምጃው ነዳጁን ከመውረስ ፈቃድ እስከመንጠቅ የሚደርስ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቀዋል። የዘገዩ ቦቴዎች መረጃ ለኮማንድ ፖስት እየተላለፈ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቀዋል። ሕገወጦች በፈጠሩት ችግር አሽከርካሪዎችና መላው ሕዝብ እየተሰቃየ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሕዝቡ በቁጥጥርና ክትትል ሥራው አሁንም ኃላፊነቱን እንዲወጣ ጠይቀዋል።

በነዳጅ ማደያዎች አካባቢም በሙሉ አቅም ያለመሥራት ችግር እንደሚስተዋል ነው ያመለከቱት፤ ይህንንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለመፍታት መሥራት አስገንዝበዋል። ቦቴዎች እርምጃዎችን በመፍራት ከተመደቡበት ቦታ ውጪ እያራገፉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነው ያረጋገጡት።

መንግሥት አንዱ ተስፋ ያደረገው ዘላቂ መፍትሔ የድጎማው መነሳት መሆኑን ይገልጻል። ነዳጁ በዓለም ዋጋ መሠረት ግብይት ሲፈጸምበት ሕገወጥ ግብይቱ በተለይ የኮንትሮባንድ ንግዱ እንደሚቀር ይጠበቃል።

በአሁኑ ወቅት ሰው ሠራሽ በሆኑ ችግሮች እየተረበሸ ያለውን የነዳጅ ገበያ ለማረጋጋትና ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚል ከሠራቸው ሥራዎች መካከል የግብይት ሥርዓቱን ዘመናዊ ማድረግ አንዱ ነው።

የግብይት ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ የታገዘ ጊዜ ቆጣቢና ቀልጣፋ በማድረግ በነዳጅ ዙሪያ እየታየ ያለውን የግብይት ችግር ለመቅረፍም የነዳጅ ድጎማ ክፍያን መፈጸም የሚያስችል መተግበሪያ ከትናንት በስቲያ ይፋ ተደርጓል። የነዳጅ ድጎማው ከሐምሌ ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረግ ችግሩ በሂደት እየተፈታ እንደሚሄድ ይታመናል።

# ከተፈጥሮ ያራቁን መተግበሪያዎች

**ዋለልኝ አየለ**

ባለፈው እሁድ ማታ «የኔ ትውልድ» የተሰኘው የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ፕሮግራም ላይ አንድ የቴክኖሎጂ ባለሙያ ሲያብራራ (ወጣት ነው) ቀልቤን ሳበውና ሙሉውን ተከታተልኩ።

ስለማህበራዊ ገጾች ሳስብ ዘላቂነታቸው ያሰጋኛል። ከሆነ ዘመን በኋላ አሁን ያለውን ለዛ የምናገኘው አይመስለኝም። ምክንያቱም ከሰዋዊነት፣ ከማህበራዊነት፣ ከተፈጥሮነት... ወደ ሮቦትነት እየተለወጥን ነው። ከባለሙያው የሰማኋቸውን ትዝብቶች ላስቀድምና ወደራሴ ትዝብት እመለሳለሁ።

ባለሙያው የመተግበሪያዎችን ፈጣን አገልግሎት ሰጪነት፣ ሥራ አቅላይነት፣ ዓለምን አቀራራቢነት ካብራራ በኋላ፤ አሉታዊ ጎናቸው ግን ተፈጥሯዊ የሆነውን «ኢንተሌጀንት» እየቀነሰብን መሆኑን ይጠቁማል። በአዕምሮ በማሰላሰል የምንሰራቸውን ሥራዎች ሁሉ መተግበሪያ ላይ ጥለናቸዋል። ምሳሌ ሲያስቀምጥም፤ በፊት ብዙ ቁጥሮችን ሁሉ እያሰብን እንደምር፣ እንቀንስ ነበር። አሁን ግን ከመቶ በታች የሆኑ ቁጥሮችን ሁሉ የምናሰላው ከስልካችን ላይ ያለውን የሂሳብ ስሌት መተግበሪያ ተጠቅመን ነው።

እነዚህን ነገሮች ለመታዘብ የባለሙያ ማብራሪያም አያስፈልገንም። በዙሪያችን ያለውን ነገር ልብ ማለት በቂ ማሳያ ነው። አሁን አሁን እያንዳንዷን ነገር በመተግበሪያ መጠቀም እየለመድን ነው። ለዚህም ነው ለትንሽ ደቂቃ ከስልካችን ስንለይ ከሕይወታችን አንድ ነገር የጎደለ የሚመስለን። በመተግበሪያዎች ምክንያት ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮችን እየረሳን ነው።

ለምሳሌ፤ ዛሬ ቀን ስንት እንደሆነ፣ የዛሬ ሳምንት ስንት እንደሚሆን፣ የነገ ወይም የትናንት ሳምንት ስንት እንደሚሆን ወይም ስንት እንደነበር ለማወቅ የራሴ የምጠቀምበት ዘዴ ነበረኝ። አሁን ግን እየረሳኋቸው ነው። ማሰብና ማሰላሰል ሳያስፈልገኝ ከስልኬ ላይ ያለውን የቀን መቁጠሪያ መተግበሪያ አያለሁ። ቀን ለማወቅ እጄ ላይ ካለው ሰዓት አያለሁ።

ከምንም በላይ ግን የሚያሰጋኝ ማህበራዊ ገጾች ከዘመናት በኋላ የአሁኑን ለዛ እና ማራኪነት ማጣታቸው ነው። እርግጥ ነው ከዘመናት በኋላ አሁን የምንጠቀምባቸው መተግበሪያዎችም ሆኑ የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች አይነታቸው ሊቀየር ይችላል። ዳሩ ግን ምንም ይሁን ምን ሰዋዊና ተፈጥሯዊ የሆነውን ነገር ካጣን ሮቦታዊ ነው የምንሆነው።

በማህበራዊ ገጾች ምክንያት ማህበራዊ ህይወታችን እየሳሳ ነው። አካባቢን ማስተዋል እየቀረ ነው። ተፈጥሮ ላይ መመሰጥና በአዕምሮ ማሰላሰል፣ መመራመር እየሳሳ ነው። ይሄ ሆነ ማለት ደግሞ በሰው ልጅ አዕምሮ ታስበው የሚሰሩ ሥራዎች ይቀንሳሉ ማለት ነው። ረጃጅም ልቦለዶች አይጻፉም ማለት ነው። ይሄ ቢቀርም ቀላል ነው ብንል እንኳን ተፈጥሮ ላይ መመራመር ይቀንሳል ማለት ነው።

ለምሳሌ፤ ኢትዮጵያዊው ሳይንቲስት ዶክተር አክሊሉ ለማ በልብስ ማጠቢያ ማሽን ልብስ ቢያጥብ ኖሮ ያንን እንዶድ ይመራመርበት ነበር? እንዶዱን ልብ ብሎ ያየው ተፈጥሮ ውስጥ ስለነበር ነው። ልክ እንደዚያ ሁሉ፤ በየደረስንበትና በያረፍንበት ሁሉ ስልክ ላይ የምናተኩር ከሆነ እነዚያን በዙሪያችን ያሉ ተፈጥሮዎች አናስተውላቸውም ማለት ነው።

ማህበራዊ ገጾች አሁን ላይ ማራኪ የሆነ ለዛ፣ ቀልብ ሳቢ የሆነ ጽሑፍ የያዙት እስከ አሁን በነበረን የማህበራዊ ሕይወት ትሩፋቶች ነው። በማህበራዊ ገጾች ቋንቋ «ሜም» የሚባሉ ቀልዶች አሉ። እነዚህን ቀልዶች ልብ ብላችሁ ካያችሁ ማህበራዊ ህይወታችን እና ግንኙነቶቻችን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። እሱ ሲረሳና ሲጠፋ እነዚህ ቀልዶች ላይኖሩ ይችላሉ ማለት ነው።

የማህበራዊ ገጾች በአገራችን ከ10 ዓመት የዘለለ ታሪክ የላቸውም። ስለዚህ አሁን ላይ ያለ ወጣት ከ10 ዓመት በፊት ተፈጥሮን ያስተውል ነበር፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ይሳተፍ ነበር፤ በአካባቢው የሚከወኑ ሁነቶችን በትኩረት አስተውሏል። ስለዚህ ዛሬ ላይ የሚጽፋቸውና የሚቀልዳቸው ሁሉ የዚያ ውጤት ናቸው።

ዛሬ ላይ ያለ አንድ የ10 ዓመት ህጻን «ስማርት» ስልክ ያዘ እንበል። ይህ ልጅ 24 ሰዓት ከዚሁ ስልክ ጋር ቢቆይ፣ ጠዋትም ማታም ከትምህርት ቤት በመኪና የሚያመላልሱት ቢሆን፣ በአጠቃላይ አካባቢውንና ተፈጥሮን የማያይ ቢሆን፤ የተፈጥሮ ተመራማሪ መሆን ይችላል? የልቦለድም ይሁን የወግ ደራሲ መሆን ይችላል? የሕዝቡንና የአገሩን ችግር ተረድቶ የፖለቲካ ጉዳዮች ተሳታፊ መሆን ይችላል?

በዚህ ልጅ ምሳሌ ከሄድን፤ ዓለም ራሱ ከሆነ ዘመን በኋላ ከተፈጥሮ ውጭ ልትሆን ትችላለች። የውጭውን ዓለም (በተለይም የምዕራባውያንን) እና የኢትዮጵያን ካነጻጸርን ደግሞ ሰፊ ልዩነት አለው። እነርሱ ከማህበራዊ ገጾች መስፋፋት በፊትም ከቡድንና አብሮነት ይልቅ ተናጠላዊ ህይወታቸው ይበዛል። ባቡር ውስጥና ባስ ውስጥ ሁሉም ጋዜጣ ነገር እያነበቡ እንደሚሄዱ አገራቱን ያዩ ሲናገሩ ሰምተናል። ስለዚህ ማህበራዊ ህይወታቸው ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ጫና እንደ ኢትዮጵያ አይሆንም።

ቀደም ሲል እንዳልኩት የሚያሳጣን የማህበራዊ ህይወት ግንኙነታችንን ብቻ አይደለም፤ ዕውቀት አጠር እንድንሆንም ያደርገናል። ተፈጥሮንና አካባቢን አንመረምርም።

ብዙ ሰዎች ማህበራዊ ገጾች ለንባብ ልምድ መዳበር ጥሩ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይናገራሉ። ዳሩ ግን ጥልቅ ንባብንና መረዳትን ያዳብራሉ ብሎ ማመን ይከብዳል። ምክንያቱም በባህሪው ፈጣን ነው፤ ብዙ ነገሮች በአንድ ጊዜ የሚታዩበት ነውና ቀልብን ወደ አጫጭር ነገሮች ይወስዉሳል።

በዚያ ላይ ማወቅ ማለት የግድ ከሚነበቡ ጽሑፎች ወይም ከሚታዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ብቻ አይደለም። ተፈጥሮን እና አካባቢያችንን በማስተዋል ብዙ ማወቅ ይቻላል። የስልካችን መተግበሪያዎች ላይ ብቻ መሆናችን ያንን ነው የሚያሳጣን።


መገናኛ ከአንድ ፎቅ ላይ ካለ የካፌ በረንዳ ላይ የተቀመጠ ሰው ስልኩን አውጥቶ ይጎረጉር ይሆናል። በስልኩም ዓለምን ያያል። ዳሩ ግን በዙሪያው ብዙ ነገሮች እያለፉት ነው። ፌስቡክ ላይ የሚያነበው እኮ ከእነዚያ አካባቢያዊ መስተጋብሮች የወጡ ናቸው። እርሱ ግን የአካባቢውን ንቆ ፌስቡክ ላይ ያለው የተሻለ ስለሚመስለው ስልኩን ይጠቀማል። የሚያስቀውም፣ የሚያስለቅሰውም ትዕይንት ግን እዚያው መገናኛ ጎዳናዎች ላይ አለ።

በዓባይ በረሃ ወደ ጎጃም የሚሄድ፣ ወይም በጊቤ በረሀ ወደ ጅማ የሚሄድ፣ ወይም በደቡብ ለምለም አካባቢዎች እያቆራረጠ ወደ አርባ ምንጭ የሚሄድ ተጓዥ ስልኩ ላይ ተደፍቶ ቢሄድ ብዙ ነገር ነው የሚያመልጠው። የተፈጥሮን ምሥጢር ማየት አልቻለም ማለት ነው፤ በየመስመሩ ዳር ያሉ ማህበረሰቦችን ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን ማየት አልቻለም ማለት ነው።

እነዚህ እንግዲህ እንደ አጠቃላይ እንደ ማህበራዊ ገጾች ካየነው ነው። በተለይ መተግበሪያዎችን ካየናቸው ደግሞ ዛሬውኑ ሮቦት ማድረግ ጀምረዋል። ሱቅ ውስጥ ትንንሽ ነገሮች ገዝተን ወይም ካፌ ውስጥ ምግብና ትኩን ነገር ተጠቅመን፤ እነዚያን ለመደመር ስልክ እናወጣለን። «አንድ አለኝ» እያሉ መደመርን፣ ከዚያኛው ቁጥር እየተበደሩ መቀነስን፣ ቁልቁል ማካፈልን እና ማባዛትን እንደ አሰልቺ ነገር ስለምናየው በጽሑፍ አንሞክረውም ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ከማሰብና ማሰላሰል እያራቀን ነው ማለት ነው።

ስለዚህ፤ ከተፈጥሯዊ ማሰብና ማሰላሰል እንዳንርቅ አጠቃቀሙን እንወቅበት!

# ዓለም አቀፍ




## የኮኬይን አደንዛዥ ዕጽ የጫኑ ሰው አልባ አነስተኛ ባህር ሰርጓጆች በስፔን ተያዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፈረንሳይ ወደሚገኙ አዘዋዋሪዎች ስለመጫኑም የተነገረላቸው ሦስት ሰው አልባ አነስተኛ ባህር ሰርጓጆች ከነያዙት የኮኬይን አደንዛዥ ዕጽ በስፔን የጸጥታ ኃይሎች መያዛቸውን ታውቋል።

የአደንዛዥ ዕጽ ማዘዋወሪያ ሦስት ሰው አልባ ባህር ሰርጓጆች አደንዛዥ ዕጹን ይዘው ከሞሮኮ መነሳታቸውን ዘጋርዲያን በዘገባው ይፋ አድርጓል።

የስፔን ፖሊስ እንዳስታወቀው ከህገ ወጥ ዝውውሩ ጋር በተያያዘ ስምንት ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል።

ወደ ፈረንሳይ ሊዘዋወር ነበር የተባለለትን ኮኬይን የጫኑት አነስተኛ ባህር ሰርጓጆች እያንዳንዳቸው 200 ኪሎ ግራም የመጫን አቅም እንዳላቸው ተነግሯል፡፡ ሆኖም ምን ያህል ኪሎ ግራም ኮኬይን ጭነው እንደተያዙ በዘገባው አልተካተተም።

በእንዲህ ዓይነት መንገድ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሲገጥሙት ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ያስታወቀው የስፔን ፖሊስ ሁኔታው ወንጀለኞች ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይፈጽሙ እየተከታተለ መሆኑን አሳውቋል።

በጅብራልታል መተላለፊያ በኩል ከሞሮኮ ስፔን ለመግባት 15 ኪሎ ሜትሮችን በሜዲትራኒያን ባህር ላይ መጓዝን ብቻ የሚጠይቅ ሲሆን፤ መስመሩ ለወንጀለኞች መተላለፊያ በመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት አካባቢ ነው።

## የሲቪል ቡድኖች በሚያደርጉት ድርድር ላይ የሱዳኑ ጦር ሠራዊቱ ተሳትፎ እንደማይኖረው አልቡርሐን አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የሱዳን ጦር ኃይል አገሪቱ ወደ ሲቪል አስተዳደር እንድትመለስ ለማድረግ ቦታውን እንደሚለቅ ወታደራዊው መሪ ጄኔራል አብዱል ፋታህ አልቡርሐን አስታወቁ።

ጄኔራሉ የሱዳን ብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ቀርበው ባደረጉት ንግግር፣ የአገሪቱ ጦር ኃይል ሱዳን ወደ ዴሞክራሲ ለምታደርገው ሽግግር እንቅፋት እንደማይሆንና ምርጫ እንዲደረግ ወስኖ እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

ጄኔራል አልቡርሐን ጨምረውም በአገሪቱ ያለውን ፖለቲካዊ ቀውስ ለማብቃት ከሲቪል ቡድኖች ጋር በሚደረገው ድርድር ላይ ጦር ሠራዊቱ የሚያደርገውን ተሳትፎ እንደሚያቋርጥ አሳውቀዋል።

ነገር ግን አገሪቱ ውስጥ ምርጫ ስለሚደረግበት እንዲሁም ጦር ኃይሉ ሥልጣን ስለሚያስረክብበት ሂደት የጊዜ ሰሌዳ ምንም ያሉት ነገር እንደሌለ ቢቢሲ በዘገባው አስፍሯል።

በሱዳን ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት የሚጠይቁት ተቃዋሚ ሰልፈኞች ሠራዊቱ ከፖለቲካው እንዲወጣ በመጠየቅ ለወራት የዘለቀ ተቃውሞ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወሳል። በመላው አገሪቱ ካለፈው ሐሙስ ጀምሮ ግዙፍ የተቃውሞ ሕዝባዊ ሰልፎች እየተካሄዱ ይገኛሉ።

ይህ የአሁኑ የጄኔራሉ ንግግርም ከሕዝቡ በገጠማቸው ተከታታይ ተቃውሞ የሰጡት ወሳኝ ምላሽ እንደሆነ ተነግሯል።

የሽግግር መንግሥቱ አካል የነበሩት የሱዳን ጦር ሠራዊት ከፍተኛ መኮንኖች ባለፈው ጥቅምት ወር በሲቪሉ የሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አብደላ ሐምዶክ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ፈጽመው ነበር ሥልጣን የተቆጣጠሩት።

የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪ የሆኑት ጄኔራል አልቡርሐን ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ በአገሪቱ ወደ ዴሞክራሲ የተጀመረውን የሽግግር ሂደት በመቀልበስ መሪነቱን ጨብጠው ቆይተዋል።

ጄኔራል አልቡርሐን ሠራዊቱ ከሚደረገው ድርድር ለመውጣት መወሰኑን ከማሳወቃቸው በፊት ባለሥልጣናት የተቃውሞ አንቀሳቃሽ ናቸው የተባሉ እና ባለፈው ዓመት ሰኔ ላይ የታሰሩ 145 ሰዎችን መልቀቃቸውን የሱዳን ዜና አገልግሎት ገልጿል።

ጄኔራል አብደል ፋታህ አል ቡርሐን በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ ለወራት ያልተቋረጠ የተቃውሞ ሰልፎች ዋና ከተማዋን ካርቱምን ጨምሮ በበርካታ የአገሪቱ ግዛቶች ውስጥ ሲካሄድ ቆይቷል።

በዚህም ለተቃውሞ ሰልፍ ከወጡ ሱዳናውያን መካከል ከ100 የሚበልጡ ሰዎች ከጥቅምት ወር ወዲህ በፀጥታ ኃይሎች መገደላቸውን የሱዳን ዶክተሮች ገልጸዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ረቡዕ ስፖርት
## አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አዲስ አበባ ከተማ ቅሬታውን እስከ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንደሚወስድ አስታወቀ

**ቦጋለ አበበ**

አጓጊ ፉክክር ያስተናገደው የ2014 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ እንደ አጀማመሩ ፍጻሜው አላማረም። በ30ኛ ሳምንት የመጨረሻ መርሐ ግብር ሶስት ጨዋታዎች በተመሳሳይ ሰዓት ሲካሄዱ የተመዘገቡ ውጤቶች ክለቦች ‹‹ከአቅም በታች ተጫውተዋል›› በሚል እርስ በርስ እየተወነጃጀሉ ይገኛሉ።

ከሻምፒዮኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ተፋልሞ 4ለ0 የተሸነፈው አዲስ አበባ ከተማ ከሊጉ መውረዱን ተከትሎ በተመሳሳይ ሰዓት በተካሄደው የፋሲል ከነማና ድሬዳዋ ከተማ የጨዋታ ውጤት ላይ ቅሬታውን እያቀረበ ይገኛል። በሌላ ወገንም አዲስ አበባ ከተማ ከአቅም በታች ተጫውቷል በሚል ቅሬታዎች ይቀርባሉ።

ይህንን ተከትሎ ከትናንት በስቲያ በኢትዮጵያ ሆቴል መግለጫ የሰጠው አዲስ አበባ ከተማ ከሊጉ የወረደው ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑን በመግለጽ ጨዋታው እንዲመረመርለት ቅሬታውን አቅርቧል። አዲስ አበባ ከተማ ራሱ ከአቅም በታች ተጫውቷል በሚል ለሚቀርብበት ወቀሳም ማስተባበያ ሰጥቷል።

‹‹በኛ ግምገማ በመጨረሻ ጨዋታ ላይ በርካታ ክለቦች በጨዋታ ማጭበርበሩ ላይ ተሳትፈዋል፣ የሐዋሳ ከተማና የአዳማ ከተማ ጨዋታም የዚሁ የጨዋታ ማጭበርበር አካል ነው›› ያሉት የከተማው ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እንዲሁም የክለቡ የቦርድ ጸሐፊ አቶ ዳዊት ትርፉ፣ አዲስ አበባ ከተማ ፍትሐዊ ውሳኔ ካልተሰጠው ምን አልባት በኢትዮጵያ እግር ኳስ የሚኖረው ተሳትፎ ሊያበቃ እንደሚችል አሳስበዋል።

አዲስ አበባ ከተማ እግርኳሳዊ ባልሆነ መንገድ ከሊጉ በመውረዱና ይህን አቅጣጫ ለማስቀየስ ሲባልም አዲስ አበባ ለጊዮርጊስ ለቋል በሚል የሚደርስበት ወቀሳ እንዳሳዘናቸውም


አዲስ አበባ ከተማ ፍትሐዊ ውሳኔ ካልተሰጠው ምን አልባት በኢትዮጵያ እግርኳስ የሚኖረው ተሳትፎ ሊያበቃ እንደሚችል በመግለጫው ተጠቁሟል፣

አቶ ዳዊት ተናግረዋል። ‹‹የመጨረሻ ጨዋታ ከመካሄዱ ከሁለት ቀን በፊት ጨዋታው በደንብ ይታይልን በሚል ለሊግ ኩባንያውና ለፌዴሬሽኑ አሳውቀናል። ክለባችን እንዲወርድ መታሰቡንም ሰምተናል፣ ከኢትዮጵያ ቡና ጋር በነበረንም ጨዋታ ብናሸንፍ አንድም ሰው በሕይወት አይተርፍም፣ ለአዲስ አበባ ክለቦች ልትለቁ በጠረጴዛ ላይ ተወያይታችሁ ነው የመጣችሁት ተብለን ዛቻ ሲሰጠንም ነበር፣ የባህርዳር የወልቂጤና የፋሲል ከነማ ደጋፊና አመራሮች ዛቻ ሲገርመን ነበር፣ ስም አልጠቅስም አታግባና አታሸንፉና ደቡብ አፍሪካ ይናፍቅሃል የሚሉ ደጋፊና አመራር ማየት ያሳዝናል›› ሲሉ አቶ ዳዊት የሂደቱን ጅማሮ ገልጸዋል።

ከዳኛ ምደባ ጀምሮ ክለቡ ጫና እንደነበረበት ያስታወሱት አቶ ዳዊት ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ መደራደር ቢፈልግ ከክለቦች ጋር መደራደር እንችል ነበር፣ ይህን ለማድረግ ግን አናስብም ለወደፊት አይታሰብም፣ በፌዴሬሽኑ 33 ድምጽ ያላቸው ክለቦች አዲስ አበባ የሚገኙ ናቸው፣ ይህን ለሀገሩ ስፖርት ትልቅ ድርሻ ያበረከተ ከተማ ለመጣል የተደረገው ሂደት አሳዝኖናል›› ሲሉ ተናግረዋል። አቶ ዳዊት አክለውም ከፌዴሬሽኑና ከአወዳዳሪው አካል ፍትሕ እንደሚፈልጉ በመግለጽ ያ የማይሆን ከሆነ በርግጠኝነት ለኢትዮጵያ እግርኳስ ፍትሕ ሲሉ እስከ ዓለም አቀፉ የስፖርት ግልግል ፍርድ ቤት እንደሚያቀኑ ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ከተማ ለጊዮርጊስ ለቋል የሚለውን ወቀሳ በተመለከተም አሰልጣኙ ጳውሎስ ጌታቸው በሰጡት ማብራሪያ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ ተጫዋቾችና አባላት ክለቡን ከመውረድ ከታደጉት የመሬትና ሌሎች አርኪ የሆኑ ጉርሻዎች ተዘጋጅቶላቸው ነበር፣ ካልወረድን የጋራ መኖሪያ ቤትና ተጨማሪ ደመወዝ ከተማ አስተዳደሩ ቃል ገብቶልን እንዴት ለጊዮርጊስ እንለቃለን›› በማለት አስተባብለዋል፡፡

የክለብ ሥራ አስኪያጅ አቶ ነፃነት ታከለ በበኩላቸው፣ ለክለቡ ከፍተኛ በጀት በከተማ አስተዳደሩ መመደቡን ገልፀው፣ ከሁለትና ከሶስት ቀናት በፊት በማኅበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁ አሉባልታዎች ቡድኑን በስነልቦና እንዳይጎዳ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንዲመራ ቢያቀርቡም ወቅታዊ ምላሽ እንዳላገኙ ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ቅሬታውን ካቀረበባቸው ክለቦች አንዱ የሆነው ፋሲል ከነማ ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዮት ብርሃኑ ‹‹በድሬዳዋ ከተማ መሸነፋችን እኛም ያልፈለግነው ነው እንጂ ታስቦበት የተደረገ ነገር እንዳልሆነ በንፁህ ልብና በሐቅ የኢትዮጵያን እግርኳስ ለሚደግፍ የስፖርት ቤተሰብ መግለፅ እንፈልጋለን›› በማለት መናገራቸው ከቀናት በፊት በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ተዘግቧል።

የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክስዮን ማኅበር የውድድርና ሥነ ሥርዓት ሰብሳቢ ዶ/ር ወገኔ ዋልተንጉስ ‹‹ይህን ድርጊት የፈፀሙና የእግርኳስ ቤተሰቡን ያሳዘኑ ክለቦች ላይ በሚቀርበው ሪፖርት ልክ እርምጃ እንወስዳለን ብለን እናስባለን፣ የተፈጠረው ክስተት በእውነቱ የእግርኳስ ቤተሰቡን ያሳዘነ ነው፤ እኛም እንደ አወዳዳሪ አካል ያዘንበት ነው፣ የጥቂት ክለብ ደጋፊዎች የእግርኳስ ድጋፍ ምን ማለት እንደሆነ እየገባቸው ያለ አይመስለኝም፣ በአንዳንድ ተፅዕኖዎች ለተወሰነ ክለቦች አድቫንቴጅ መስጠትን የሚያሳዩ ነገሮች ተከስተዋል፣ፕሮፌሽናል አስተሳሰብ እስካልሰረፀ ድረስ አሁን የተከናወነውን ነገር በቅጣትና በማስተማር የሚመለስ መስሎ አይታየኝም›› በማለት ለሶከር ኢትዮጵያ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሐፊ አቶ ባህሩ ጥላሁን በበኩላቸው ጉዳዩ ተጣርቶ ፌዴሬሽኑ እርምጃ የማይወሰድበት ወይንም ህጋዊ ነገር የማይደረግበት ምንም ምክንያት እንደማይኖር ከሶከር ኢትዮጵያ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር የውድድርና ሥነሥርዓት ኮሚቴ በ30ኛ ሳምንት የሀዋሳ ከተማና የአዳማ ከተማ፣ የድሬዳዋ ከተማና የፋሲል ከነማ እንዲሁም የቅዱስጊዮርጊስና የአዲስ አበባ ከተማ ጨዋታ የሚመለከታቸውን አመራሮች፣ አሰልጣኞች፣ ዳኞችና ኮሚሽነሮችን በዛሬው እለት በተለያየ ሰዓት ለማናገር ቀጠሮ መስጠቱ ታውቋል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# “ሲንቄ/ሲቆ” ባህል ላይ ያተኮረው የምርምር መጽሐፍ

የገዳ ሥርዓት በኦሮሞ ሕዝብ የረዥም ዕድሜ አደረጃጀት ውስጥ ጉልህና እና ዋነኛ ድርሻ ያለው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የማኅበረሰብ አኗኗር አስተዳደር የረቀቀ ጥበብ ነው። የኦሮሞ ሴቶች የእርቅና የሰላም ተምሳሌት የሆነው “ሲንቄ/ሲቆ” ደግሞ ለዓለም ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ከገዳ ሥርዓት አንዱ ነው።

በኦሮሞ ባህል ዘንድ ከፍተኛ ሚና ያለው “ሲንቄ/ሲቆ” ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው። የዲሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ በሆነው የገዳ ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ አንዱ የሆነው የግጭት መፍቻ፣ የጾታዊ ጥቃት መከላከያ፣ የሴቶች የሰላም ጦር በመባል የምትታወቀውን ተምሳሌታዊ የ”ሲንቄ/ሲቆ” ባህላዊ ሥርዓት ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ በሴቶች የሚከወን የግጭት አፈታት ሥርዓት ነው። የሰላም በትር በመሆኑም የሴቶችን መብት በማስከበር ለዓለም ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ከገዳ ሥርዓት አንዱ ነው።

“ሲንቄ/ሲቆ” ባህላዊ ሥርዓት ሴቶች በስፋት በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ትኩረት የሚያሳዩበት የገዳ ሥርዓት ሲመሠረት አብሮ የተመሠረተ ነው። የገዳ ሥርዓት ሲመሠረት ለአባ ገዳው “ሎጋ” ቦኩ እና ከለቻ” ለሴቷ ደግሞ “ሲንቄ፣ ጫንጮ እና ጭጮ” በተለያዩ ክብረ በዓላትና ውሳኔ በሚሰጡበት ቦታዎች ላይ እንዲጠቀሙበት የገዳ ሥርዓቱ ደንግጓል።

“ሲንቄ/ሲቆ” “ሀሮሬሳ” ከሚባል እና ከሌሎች ከማይነቅዙ ከተመረጡ የዛፍ አይነቶች ተቆርጣ የምትዘጋጅ ቀጥ ያለችና ያልተጣመመች ዘንግ ወይም በትር ስትሆን የጋብቻ እለት እናት ለምትድራት ልጇ የምትሰጣት እስከ እለተ ሞቷ የማትለያት የክብር መገለጫ ስጦታዋ ናት።

ይህች የሰላም ጦር የሚዋጉባት ሳይሆን ክብራቸውን የሚያስጠብቁባት፣ ሰላምን የሚያወርዱባት፣ ፈጣሪን የሚለምኑባት፣ አባ ገዳዎች ሲሾሙና ወንዶች ወደ ጦር


የመጽሐፉ ምረቃ ሥነ-ሥርዓት፤

ሜዳ ሲሄዱ ድል እንዲቀናቸው የሚመርቁባት፣ ጋብቻንና ጉዲፈቻን ሕጋዊ የሚያደርጉባት፣ ሥልጣን የሚጋሩባት እና ሀብት የሚያገኙባት ከገዳ ሥርዓት ጋር ተያይዛ የምትሄድ ለሴቷ ተብላ የተደነገገች በሴቶች ብቻ የምትከናወን ባህላዊ ሥርዓት ናት።

ይህንን የኦሮሞ ሴቶች የእርቅና የሰላም ተምሳሌት የሆነውን የኢትዮጵያ ባህል ለዓለም ለማስተዋወቅ “ሲንቄ/ሲቆ” ባህላዊ ሥርዓት ምንነት እና በኦሮሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን ሚና የሚዳስስ መጽሐፍ ከሰሞኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለሕትመት በቅቷል። መጽሐፉ “THE ESSENCE OF SINQE/SIQQO CULTURAL SYSTEM AND ITS ROLE IN THE OROMO COMMUNITY ” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን፤ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋራ በመተባበር በጋራ አሳትመውታል።

በመጽሐፉ ምርቃት ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ እንደገለጹት፤ የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት “ሲንቄ” ባህላዊ ሥርዓት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። ስለዚህ “ሲንቄ” ሴቶች ነጻነታቸውንና መብታቸውን የሚያስከብሩበት፤ማኅበራዊ ኃላፊነት የሚሸከሙበት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ባህላዊ ሥርዓት ነው። መንግሥት እንደ “ሲንቄ”ያሉ ባህሎችን የመጠበቅና የማበልጸግ ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘመናዊ ትምህርት ውስጥ በማካተት ለትውልዱ ማሳወቅ እንደሚገባም ይጠቁማሉ። “ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዙ ባህሎች የበለፀገች ስትሆን ከነዚህም አንዱ የገዳ ስርዓት በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እና አሁንም እየተተገበረ ያለ ነው” ያሉት ሚኒስትሩ፤ የምርምር ተቋማትም ባህላዊ እሴቶችን በማጥናት ሀገራዊ ፋይዳቸውን ሊያሳድጉ እንደሚገባም ይናገራሉ። “ሲንቄ/ሲቆ” የነፃነት፣ የመብትና የሰላም ምልክት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሚኒስቴሩ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህልና ቋንቋ ለማጥናት፣ ለመንከባከብና ለማስተላለፍ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል የኦሮሞ ሴቶች በማኅበረሰባቸው ውስጥ የባህል፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኃይማኖታዊ ሚና ሊጫወቱ ከሚችሉ ቁሳዊ ባህሎች መካከል አንዱ “ሲንቄ” ስለመሆኑ የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገልጸው፤ “ሲንቄ” የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ባህል መሆኑን ያመለክታሉ።

“ሲንቄ” ለሰላም እና ለግጭት አፈታት ሴትን የማብቃት ምልክት ሆኖ የሚያገለግል ልዩ ሥርዓት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ሲወርድ ሲዋርድ በማኅበራዊ ደረጃ የተረጋገጠ የመብት ስብስብን የሚያመለክት የተቀደሰ በትር ስለመሆኑም በንግግራቸው በአፅዕኖት ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን በማረጋገጥ የሴቶችን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መብትና ጥቅም የሚያስከብሩ ተቋማት ሊበረታቱ እንደሚገባ ሚኒስትሯ ጠቁመው፤ ሚኒስቴሩ የፖሊሲ ክለሳ እያደረገ ይገኛል። በክለሳው ውስጥ በ”ሲንቄ”ና ሌሎች ባህሎች ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ሀገር በቀል እውቀቶችን ለማካተት እየተሠራ መሆኑን ይገልፃሉ።

የዩኔስኮ ተወካይ የሆኑት አቶ ጌቱ አሰፋ በበኩላቸው፤ በኦሮሞ ማኅበረሰብ የገዳ ሥርዓት ውስጥ “ሲንቄ” ለሰላም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን ገልፀው፤ በማይዳሰሱ ቅርሶች ላይ ተመዝግቦ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንዳለ ይናገራሉ።

በመጽሐፉ ዝግጅት ሂደት የተሳተፉት ወይዘሮ ወይንሸት ሀብተማሪያም በበኩላቸው፤ “ሲንቄ” ባህል በስፋት በሚተገበርባቸው በኦሮሚያ አራት ዞኖች ጥናት በማካሄድ መጽሐፉ መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ የመጽሐፉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መታተም የኢትዮጵያን ባህል ለዓለም ከማስተዋወቅ በላይ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ያሉ በርካታ ባህሎችን ለማበልጸግና ለማሳደግ መነሳሳትን እንደሚፈጥር ያስረዳሉ።

በመጨረሻም በመድረኩ በመጽሐፉ ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ አምባሳደሮች፣ አባ ገዳዎች፣ አደ “ሲንቄ/ሲቆ” እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ሥነ- ሥርዓት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የ”ሲንቄ/ሲቆ” የምርምር መጽሐፍ በይፋ ተመርቋል።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia